«እግዚአብሔር የሚመጣባትን ፥ ሰማያትም ቀልጠው የሚጠፉባትን፥ ፍጥረትም ሁሉ ተቃጥሎ የሚጠፋባትን ዕለት በተስፋ እየጠበቃችሁ ፍጠኑ። እኛ ግን ጽድቅ የሚኖርባቸውን አዲሶቹን ሰማያትና አዲሲቱን ምድር ተስፋ  እናደርጋለን።»

*፪ኛ ጴጥ ፫፥፲፪—፲፫*

# ስምዐ ጽድቅ



## ማውጫ


፪ አጫጭር ዜናዎች

፬ መልእክት

፮ ሪፖርታዥ

፱ ቤተ አብርሃም

፲፫ ቃለ መጠይቅ

፲፮ የሕፃናት ዓምድ

፲፰ ትዝብት

፳ ምሥጢሬን ላካፍላችሁ



## ስምዐ ጽድቅ

የቤተ ክርስቲያኒቱን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓትና ትውፊት ጠብቆ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ማኅበረ ቅዱሳን በትምህርትና ሐዋርያዊ አገልግሎት ማስተባበሪያ በጋዜጣ ዝግጅት ክፍል እየተዘጋጀ በወር ሁለት ጊዜ የሚወጣ መንፈሳዊ ጋዜጣ

ጳጉሜን ፫ ቀን ፲፱፻፹፭ ዓ.ም. ተጀመረ



☎ 011-1553555/ 011-1553442

✉ 80078

አዲስ አበባ

የዝግጅት ክፍሉ ኢሜይል
newspaper@eotcmk.org

ምክትል ዋና አዘጋጅ
ወርቅነሽ ቱፋ

ከፍተኛ ሪፖርተር
ካሣሁን ለምለሙ

ሪፖርተር
ረቂቅ መቻል

የገጽ መልክ (Layout) ዲዛይነር
ግደይ ገብሬ

ጸሐፊ
ገነት ታደሰ

# ምእመናን ፍትሕን የሚያሰፍን የፖለቲካ ድርጅት እንዲመርጡ ማኅበሩ አሳሰበ

*በካሣሁን ለምለሙ*

ምእመናን በሀገራችን ኢትዮጵያ ፍትሕ ርትዕን የሚያሰፍን የፖለቲካ ድርጅት ሊመርጡ እንደሚገባ በኢ/ኦ/ተ/ቤ የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳን ዋና ጸሓፊ አቶ ውብሸት ኦቶሮ አሳሰቡ፡፡

ኦርቶዶክሳውያን ምእመናን በሀገራቸው ፍትሕ ርትዕን የሚያመጣ የፖለቲካ ድርጅት እንዲመርጡ ማኅበረ ቅዱሳን የድርሻውን እንደሚወጣ ያስታወቁት ዋና ጸሐፊው ምርጫ ላይ ባለመሳተፋቸው በቤተ ክርስቲያን ላይ ሊመጣ የሚችለውን ጫና እንዲረዱ የማድረግ ሥራ እንደሚሠራም ተናግረዋል፡፡ ቤተ ክርስቲያናችን ከዚህ ቀደም በሀገራችን ፖለቲካ ላይ በበቂ ሁኔታ ባለመወከሏ ላለፉት በርካታ ዓመታት ግፍ ሲፈጸምባት እንደኖረች አክለዋል፡፡

ላለፉት በርካታ ዓመታት በቤተ ክርስቲያንና በምእመናን ላይ ሲፈጸጸም የቆየውን በደል የፖለቲካ ድርጅቶች ድምፅ እንዳላሰሙ እንዲሁም ግፉን እንዳላስቆሙ ያስታወሱት ዋና ጸሓፊው ይህ ችግር ዳግም እንዳይከሠት፣ የቤተ ክርስቲያንና የምእመናን ድምፅ የሚሰማበት ዘመን እንዲመጣ ምእመናን በቀጣዩ ስድስተኛው ሀገራዊ ምርጫ ላይ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ መክረዋል፡፡

ይሁን እንጂ የሥራ አመራር አባላት፣ የሥራ አስፈጻሚ አባላት፣ ማእከላት፣ ወረዳ ማእከላት እንዲሁም የግቢ ጉባኤያት አመራሮች የፖለቲካ ተሳትፎ ማድረግ እንደማይችሉ የማኅበሩ የሥራ አመራር መመሪያ በክልከላ ያስቀመጠ መሆኑን ዋና ጸሓፊው አያይዘው ተናግረዋል፡፡



አቶ ውብሸት ኦቶሮ በኢ /ኦ /ተ /ቤ የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳን ዋና ጸሐፊ

ከማኅበሩ አገልግሎት ከለቀቁ የቆዩ የቀድሞ አመራሮች ደግሞ እነሱ ከፈለጉ የፖለቲካ ተሳትፎ ማድረግ እንደሚችሉ እና በአሁኑ ሰዓት በፖለቲካው ውስጥ ያሉ ደግሞ ከላይ በዝርዝር ክልከላ ከተደረገባቸው የማኅበሩ የአገልግሎት ዘርፎች ውጭ ማገልገል እንደሚችሉ ዋና ጸሐፊው አስረድተዋል፡፡

ምእመናን በፖለቲካ ውስጥ መሳተፋቸው ከማኅበረ ቅዱሳን አገልግሎት ሊያርቃቸው እንደማይችል ያስረዱት ዋና ጸሓፊው ከኦዲትና ኢንስፔክሽን፣ ሚዲያ ክፍልና ኤዲቶሪያል ቦርድ ውጭ ባሉ የማኅበሩ የአገልግሎት ዘርፎች ውስጥ የሚያገለግሉበት ሂደት መመቻቸቱን አስረድተዋል፡፡

በመጨረሻም ኦርቶዶክሳውያን የፖለቲካ ተሳትፎ እንዳያደርጉ የሚከለክል መመሪያ እንደሌለ ተረድተው በወደዱና በመረጡት የፖለቲካ ድርጅት ውስጥ በመሳተፍ ሀገራቸውን፣ ቤተ ክርስቲያናቸውንና ምእመናንን የሚያገለግሉበትን ዕድል እንዲፈጥሩ ጥሪ ያቀረቡት ዋና ጸሓፊው ‹‹የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ ብቻ ተመርጦ ሀገር መምራት አለበት የሚል እምነት የለንም፤ ሆኖም ግን ሀገርን የሚያስተዳድረው አካል እምነቱ ምንም ይሁን ምን በፍትሐዊነትና በእኩልነት ሊመራ ይገባዋል›› ብለዋል፡፡



ብፁዕ (ዶ/ር) አቡነ ጢሞቴዎስ

# የብፁዕ (ዶ/ር) አቡነ ጢሞቴዎስ ሥርዓተ ቀብር ተፈጸመ

*በጋዜጣው ሪፖርተር*

የብፁዕ አቡነ ጢሞቴዎስ ሥርዓተ ቀብር ረቡዕ መጋቢት ፳፱ ቀን ፳፻፲፫ ዓ.ም በመንበረ ጸባኦት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ተፈጸመ::

ብፁዕ አቡነ ጢሞቴዎስ (ዶር) ከአባታቸው ከባላምባራስ ተስፋ ተክሉ እና ከእናታቸው ከወይዘሮ ታህሣ ኃይሉ በግንቦት ወር ፲፱፻፴ ዓ.ም በትግራይ ክልል ብዛታ ወረዳ ፍልፍሎ መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን አካባቢ እንደተወለዱ የሕይወት ታሪካቸው ያስረዳል:: ዕድሜያቸው ለትምህርት እንደረሰም በተወለዱበት አካባቢ ከአባታቸው ወንድም አባ ገብረ አረጋዊ ፊደል ንባብ የቃል ትምህርት ተምረዋል:: በአቡነ ሳሙኤል ዘደብረ ሃሌ ሉያ ገዳም ከመምህር ገብረ እግዚአሔር መዝገበ ቅዳሴን፣ ከመሪጌታ ይትባረክ ጸዋትወ ዜማን አጠናቀው የተማሩ ሲሆን በጎጃም ጠቅላይ ግዛት እነማይ አውራጃ መንግሥቶ ቅድስት ኪዳነ ምሕረት ከመምህር ደጉ ቅኔን ከነ አገባቡ አጠናቀዋል::

ብፁዕ (ዶ/ር) አቡነ ጢሞቴዎስ የመጀመሪያ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በሀገር ውስጥ ጨርሰው ለሁለተኛና ለሦስተኛ ዲግሪያቸው ወደ ራሽያ (የቀድሞው ሶቪየት ኅብረት) በመሄድ ከሌሊንግራድ ዩኒቨርሲቲ የዶክተሬት ዲግሪያቸውን ተቀብለዋል::

ብፁዕነታቸው በ፲፱፻፵፪ ዓ.ም መዓርገ ዲቁናን የኤርትራና ትግራይ ክፍለ ሀገር ሊቀ ጳጳስ ከነበሩት ከብፁዕ አቡነ ማርቆስ እጅ፣ በ፲፱፻፵፮ ዓ.ም፣ መዓርገ ምንኵስናን በአቡነ ሳሙኤል ዘደብረ ሃሌ ሉያ ገዳም፣ በ፲፱፻፵፯ ዓ.ም መዓርገ ቅስናን ከብፁዕ አቡነ ማርቆስ የቀድሞው የኤርትራና የትግራይ ሊቀ ጳጳስ እንዲሁም በ፲፱፻፸፱ ዓ.ም በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት አንብሮተ እድ ብፁዕ አቡነ ጢሞቴዎስ ተብለው ተሹመዋል::

ብፁዕ (ዶር) አቡነ ጢሞቴዎስ ከልጅነታቸው በግብረ ዲቁና የጀመሩትን አገልግሎት በገዳም በረድዕነት፣ በመጋቢነት በመምህርነት እና በአፈ መምህርነት፤ በሰዋሰወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ መንፈሳዊ ት/ቤት በዳይሬክተርነት፣ በቤተ ክህነት ትምህርት ክፍል ኃላፊነት፣ በገዳማት መምሪያ ኃላፊነት ያገለገሉ ሲሆን መዓርገ ጵጵስና ከተቀበሉ በኋላ በቅዱስ ሲኖዶስ ምክትል ኃላፊነትና ጸሓፊነት፣ በመንበረ ጸባኦት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል በሊቀ ሥልጣንነት፣ በትንሣኤ መጻሕፍት ማሳተሚያ ድርጅት በዋና ኃላፊነት፤ በሰበታ ቤተ ደናግል በበላይ ኃላፊነት፤ በውጭ ጉዳይ መምሪያ ኃላፊነት፣ በክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን በኃላፊነት፣ በከፋ፣ማጂ፣ኩሎ ኮንታ በሊቀ ጳጳስነት እንዲሁም በቅድስት ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ በበላይ ኃላፊነት ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ አገልግለዋል::

ብፁዕነታቸው ከ፳፻፲፪ ዓ.ም ጀምሮ በቅዱስ ሲኖዶስ ፈቃድ በጸሎትና በቡራኬ ሆነው በቅድስት ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ባለ ሙሉ ሥልጣን ረዳት ሊቀ ጳጳስ ተመድቦላቸው የበላይ ጠባቂ ሆነው እያገለገሉ ይገኙ ነበር::

በተወለዱ በ፹፫ ዓመታቸው ከዚህ ዓለም ድካም ያረፉት ብፁዕ (ዶ/ር) አቡነ ጢሞቴዎስ ሥርዓተ ቀብራቸው ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት፣ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትና ኤጲስ ቆጶሳት እንዲሁም የመንፈስ ቅዱስ ልጆቻቸው በተገኙበት በመንበረ ጸባኦት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል በክብር ተፈጽሟል::

# በመጪው ሀገራዊ ምርጫ የምእመናን ተሳትፎ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሀገርን በሚመለከት ማንኛውም ጉዳይ ላይ ዘርፈ ብዙ አገልግሎት ስትሰጥ ቆይታለች። ተደጋግሞ እንደሚጠቀሰው የትምህርት ሚኒስቴር፣ የገንዘብ ሚኒስቴር የማስታወቂያ ሚንስቴር፣ የመንፈሳዊ ፍርድ ቤት ሆና ሀገርን እና ሕዝብን ስታገለግል ኖራለች። ኦርቶዶክሳውያን ልጆቿም ከቤተ መንግሥት ጀምሮ እስከታችኛው የአስተዳደር መዋቅር ድረስ በሀገራችን በተለያዩ መሥሪያ ቤቶች ውስጥ በከፍተኛ ኃላፊነት፣ በአማካሪነት እንዲሁም በዲፕሎማትነት ሲያገለግሉ ኖረዋል። እነዚህ ሁሉ ቤተ ክርስቲያን በሀገር ላይ ለነበራት ከፍተኛ ሥፍራ እና ተሰሚነት ማሳያዎች ናቸው።

በሀገራችን ውስጥ የሚገኙ ተቋማትም ሆኑ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች የኋላ ታሪካቸው ሲታይ የቤተ ክርስቲያን አሻራ ያረፈባቸው ናቸው። በእምነት ተከታዮቿ ብዛት የሀገራችን ሕዝብ ከግማሽ በላይ የሚሸፍን ምእመን ያላት ክርስቶሳዊት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ታላቅ ክብርና ተሰሚነት የነበራት፣ ታላቅ ቦታም የሚሰጣት ተቋም ነበረች። እንደዛሬው ሳይሆን በዚህ ወቅት በታላቁ የጾመ ሁዳዴ የመገናኛ ብዙኃኑ ሳይቀር ስለመንፈሳዊ ነገር የሚሰብኩ፣ በዘፈን ፈንታ የበገና መዝሙር የሚሰማባቸው ነበሩ።

የዘውዳዊው ሥርዓት ሰፍኖ እስከቆየበት እስከ ፲፱፻፷፯ ዓ.ም ድረስ ቤተ ክርስቲያን በሀገሪቱ ውስጥ ሚሶ መንግሥት ነበራት፤ ንግሥናውም ተዋረዳዊ (ሰሎሞናዊው ሥርዓተ መንግሥት) በመሆኑ ነገሥታቱን በቅብዐ መንግሥት የምታነግሥው እንዲሁም ለንግሥናው ቡራኬ የምትሰጠው ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ነበረች። በአጠቃላይ በሀገር የዕለት ከዕለት እንቅስቃሴ ውስጥ ቤተ ክርስቲያን ነበረችበት። በቤተ ክርስቲያን በሚደረጉ ታላላቅ ክብረ በዓላት ላይ ሁልጊዜ ነገሥታቱ ከቅዱስ ፓትርያርኩና ከሊቃነ ጳጳሳቱ ጎን ነበሩ። ፓትርያርኩና ሊቃነ ጳጳሳቱም በተመሳሳይ በቤተ መንግሥቱ በነበሩ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ የነበራቸው ንቁ የአብሮነት ተሳትፎ እንደዚያው ነበር።

በእነዚያ ዘመናት ቤተ ክርስቲያን በአንጻራዊነት ለራስዋ አስተዳደራዊ አገልግሎት የምትጠቀምባቸው የእርሻ መሬቶች ነበሯት። በዚህም መሠረት ሌሎች አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናትን ለመትከልም ሆነ መንፈሳዊ አገልግሎትን ለመፈጸም ብዙ ችግር አልነበረባትም። ምክንያቱም ነገሥታቱ ራሳቸው የቤተ ክርስቲያንን ሥርዓት የማይጋፉ ክብርና መብትዋንም አስጠብቀው የሚሠሩ ስለነበሩ ተሰሚነትዋ ከፍ ያለ ነበር። በ፲፱፻፷፯ ዓ.ም የዘውዳዊውን ሥርዓት መንበረ ሥልጣን በኃይል የነጠቀው የደርግ መንግሥት ሥልጣኑን ሲረከብ የቤተ ክርስቲያን ዕጣ ፈንታና ክብር ከዘወዳዊው ሥርዓት ጋር አብሮ ወደቀ። በውጭ ወራሪ ሳይሆን በሀገር ልጆች ፓትርያርኳን በሞት ተነጠቀች። አድሃሪ ናት ተብላ የምትተዳደርበት ንብረት ሳይቀር እንዲወረስ ሲደረግ ወደ ድህነት አሽቆልቁላ በዐውደ ምሕረቷ ላይ ቆማ እንድትለምን ተገደደች። እስከ ዛሬም ጠባሳው አልጠፋም።

ደርግ ወድቆ የኢሕአዴግ መንግሥት ቦታውን ቢይዝም የቤተ ክርስቲያን ጉዳይ ከድጡ ወደ ማጡ ሆነ እንጂ የተሻለ ነገር አልታየበትም። ቤተ ክርስቲያን በዘመናት ውስጥ ስትገፋ፣ ያላትን ሁሉ ስትነጠቅ፣ ስታጣ ኖራለች። ለዚህ ሁሉ ዓይነተኛው ምክንያት በሀገሪቱ ውስጥ ባሉ ታላላቅ ተቋማት የሚቀረቀርላት፣ ለምን ብሎ የሚጠይቅላት፣ የተበላሸውን የሚያስተካክልላት ሰው አለመኖሩ ነው። በሌሎች እምነቶች

# መልእክት

ዘንድ በዓላማ የሚገባባቸው የተለያዩ ፖለቲካ ቀመስ ሀገራዊ ተቋማት በቤተ ክርስቲያን ልጆች ግን የሚፈሩና ‹‹ፖለቲካን በሩቁ›› ተብለው የሚራቁ መሆናቸው ነው፡፡ ገፍተው የሄዱት እና በከፍተኛ የሥልጣን እርከን ላይ ያሉ የቤተ ክርስቲያን ልጆችም ቢሆኑ ለተቀመጡበት ወንበር ከማገልገል ውጪ እንደ ቤተ ክርስቲያን ልጅነታቸው ጎን ለጎን የቤተ ክርስቲያንን ክብር ለማስጠበቅ አልታደሉም፡፡ ብዙዎቹ ሥልጣን በክርስትናቸው ላይ አጥልቶባቸው ተሸፍነው ቀርተዋል፤ ሰማያዊውን ሳይሆን ምድራዊውን ብቻ ሲያገለግሉ ኖረዋል፡፡

በዘመነ ኢሕአዴግ ተጠናክሮ በመጣው የምርጫ ሥርዓት ላይ ለመሳተፍም የቤተ ክርስቲያን ልጆች ቸልተኝነትን ማሳየታቸው ዛሬ ዋጋ እያስከፈለን ይገኛል፡፡ ሀገር የሁሉም፤ ሁሉም በእኩልነት የሚኖርባት እንዲሁም ሁሉም በእኩልነት የሚመራት መሆኑ እሙን ቢሆንም ድርሻችንን አሳልፈን መስጠታችን የበይ ተመልካች ብቻ ሳይሆን ነፃነታችንን አሳልፈን እንድሰጥ አድርጎናል፡፡ እኛ የጣልነውን መብት ሌሎች አንሥተው ራሳቸውን ሲጠቅሙበት እኛንም ሲጎዱበት ለምን ብሎ መጠየቅ ከእያንዳንዱ ክርስቲያን ይጠበቃል፡፡ ‹‹ሀገር ናት›› የተባለች ኦርቶዶክስ ሀገር አልባ ሆና በብዙ ስትገፋ ሀገር መሆንዋን የሚያሳዩ ብርቱ ልጆች ሊሆኑ ይገባ ነበር፡፡ ዛሬ ግን ከመቼውም ይልቅ ወቅቱ የሚጠይቀው ጉዳይ ራስን በሁሉም ሀገራዊ ጉዳዮች ተሳታፊ ማድረግ ነው፡፡

ነገ እና ከነገ ወዲያ ቅድስት የሌቦችና የወንበዴዎች የግፈኞችም መናኸሪያ ሳትሆን በቀደመ ክብርዋና ልዕልናዋ የኦርቶዶክሳውያን ቤት ሆና እንድትቀጥል ዛሬ ላይ ልጆቿ ተግተው ሊሠሩ ይገባል፡፡ የትላንቱ ቸልተኝነት ዛሬ ቤተ ክርስቲያን ስጥቃጠል፣ ስትዋረድ፣ ስትሰደድ ቆመን እንድናይ እያደረገን ነውና ልብ ብለን የነገ የቤት ሥራችንን ልንሠራ ይገባል፡፡ ትላንት ደፍረው ወደ ፖለቲካው መድረክ የመጡ የቤተ ክርስቲያን ልጆች ሲገፉ፣ ሲዘበትባቸው ‹‹ክርስቲያንና ፖለቲካ›› በሚል ሽፋን በፍርሃት እንዲኖሩ መደረጋቸው ወደዚያም የሚገባ ኦርቶዶክሳዊ አማኝ እንዳይኖር፤ የገቡትም ሐሜትና ስድብን ሽሽት ከቤተ ክርስቲያን እንዲርቁ እንቅፋት ሆኖ ዘልቋልና ትናንትን ላለመድገም ዛሬ ላይ ልጆቿ ጠንክረው መሥራት ይጠበቅባቸዋል፡፡

ሀገርም ሆነች ቤተ ክርስቲያን የሁላችን ናትና ነገ በጠንካራ መሠረት ላይ የቆመች የማትነቃነቅ እንድትሆን የድርሻችንን ልንወጣ ይገባል፡፡ ሀገር ከፍ ብላ እንድትታይ በውስጧ የሚኖሩ ሁሉም ዜጎች መብቶቻቸው ይከበሩላቸው ዘንድ አጥብቆ የሚሠራ እንዲሁም የተሻለ ርዕዮተ ዓለም ያለውን የፖለቲካ ድርጅት መምረጥ ችላ የማይባል ትልቅ ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ሀገርን ለመምራት ራስን ማዘጋጀት፤ ቤተ ክርስቲያንን ከተጋረጠባት ፈተና ለመታደግ፤ እንዲሁም በፈረሰው በኩል ለመቆም ራስን ለዕጬነት ማቅረብ፣ ለዚያ መዘጋጀት ሁለት አፍ ያለው ሰይፍ መሆን ነውና በእጅጉ ሊታሰብበት ይገባል፡፡

ሀገር የእነ እገሌ ብቻ ሳትሆን የኛም ናት በሚል የተቆርቋሪነት ስሜት ነገን ዛሬ መሥራት ከእኛ ከክርስቲያኖች የሚጠበቅ ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያን እና ልጆቿ ሀገርን ጠብቀው ማቆየታቸውን የትላንት ብቻ ታሪክ አድርጎ ማለፍ አይገባም፡፡ ነገን በተሻለ ለመሥራት ዕድሉ ዛሬ በእጃችን ነውና ልንጠቀምበት ይገባል፡፡ መመረጥም ሆነ መምረጥ ለሌሎች የምንተወው ጉዳይ ሳይሆን ጠበቅ አድርገን ልንይዘው የሚገባ ነውና ለዚያ መዘጋጀት ተገቢ ነው እንላለን፡፡

# ፍትሕን የተጠሙ ነፍሳት...

በካሣሁን ለምለሙ

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንና በምእመናን ላይ ከሌላው ጊዜ በተለየ መልኩ መጠነ ሰፊ የሆነ የአካል፣የንብረት፣የሥነ ልቡናና የኢኮኖሚ ጥቃት እየተፈጸመባቸው ይገኛል፡፡ ጥቃቱን በአብዛኛው የሚፈጽሙት በሃይማኖት ስም የተደራጁ አክራሪ ቡድኖች ናቸው፡፡ በተለይም በአንዳንድ የኦሮምያ ክልል ከተሞች በተደራጀና በተቀናጀ መልኩ የማያቋርጥ ውድመትና ጭፍጨፋ ሲያደርሱ ቆይተዋል፤ አሁንም እያደረሱ ይገኛሉ፡፡ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት እነዚህ ጽንፈኛ አክራሪ ኃይሎች ከሀገር ውስጥና ከውጭ ሀገራት ጭምር ሳይቀር የስንቅና ትጥቅ ድጋፍ ይደረግላቸዋል፡፡

ለአክራሪ ጽንፈኛ ኃይሎች የስንቅና ትጥቅ የሚያቀርቡትም ሆነ የአክራሪዎቹ ዋና ዓላማ ቤተ ክርስቲያንን ማዳከም ሕዝበ ክርስቲያኑን ደግሞ ቢችሉ እነርሱ ወደሚፈልጉት እምነት መውሰድ ካልሆነ ደግሞ መግደል፣መዝረፍ ማፈናቀል እንዲሁም ሕይወታቸውን በስጋትና በሰቀቀን እንዲገፉ ማድረግ ነው፡፡ የመጨረሻ ሕልማቸውም ወድቃ የማትወድቀውን ቤተ ክርስቲያንን ገፍተው መጣል ነው፡፡ ይህንን ተግባር ላለፉት አርባና ኀምሳ ዓመታት ይፈጽሙት እንደነበረ ቢታወቅም በተለይ ካለፉት ሦስት ዓመታት ወዲህ መልኩንና ዓይነቱን እየለዋወጡ በቤተ ክርስቲያንና በምእመና ላይ ዘመን የማይሽረው ትውልድ የማይረሳው በደል ሲያደርሱ ቆይተዋል፤ አሁንም እያደረሱ ይገኛሉ፡፡

በኦሮምያ ክልል አንዳንድ አካባቢዎች በቤተ ክርስቲያንና በምእመናን ላይ እየተፈጸመ ከላው መጠነ ሰፊ ጥቃት ባልተናነሰ መልኩ በሌሎች የሀገሪቱ ክፍሎችም ኦርቶዶክሳውያንን ዒላማ ያደረገ ጥቃት ተፈጽሟል፡፡ በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የብዙኃንን ትኩረት እየሳበ የመጣው በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በሰሜን ሸዋ ሀገረ ስብከት በተደጋገሚ በኦርቶዶክሳውያንና በቤተ ክርስቲያን ላይ እየተፈጸመ ያለው ግድያና ዘረፋ ነው፡፡ በዚህ ሀገረ ስብከት ለበርካታ ዓመታት ኦርቶዶክስ ተኮር ጥቃት ሲሰነዘር ቢቆይም ባለፉት ሦስት ዓመታት አክራሪዎች በተከታታይ የፈጸሙት ጥቃት ግን የተለየ ነው፡፡ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የሰላም ሕዝብ ደኅንነት ጉዳዮች ቢሮ ኃላፊ አቶ ሲሳይ ዳምጤ በሰሜን ሸዋና በኦሮሞ ብሔረሰብ ዞኖች  መጋቢት ፲ ቀን ፳፻፲3 ዓ/ም በተነሣ የፀጥታ ችግር በሰው ሕይወትና በንብረት ላይ ጉዳት መድረሱን መጋቢት ፲፪ ቀን ፳፻፲፫ ዓ/ም ለአማራ ብዙኃን መገናኛ ድርጅት ተናግረዋል፡፡

ስለሆነም በጥቃቱ ሳቢያ በኦርቶዶክስ ክርስቲያኖችና በቤተ ክርስቲያን ላይ የደረሰውን ጥፋት፣ ዓይነትና የጉዳት መጠን ለማጠራት የሀገረ ስብከቱን ሥራ አስኪያጅና የዞኑን አስተዳደሪ መረጃ ጠይቀን የሚከተለውን ጽሑፍ አጠናቅረናል፡፡

የሰሜን ሸዋ ሀገረ ስብከት ሥራ አስኪያጅ መጋቤ ሐዲስ ነቅዐ ጥበብ አባቡ ከዝግጅት ክፍላችን ጋር በስልክ በነበራቸው ቆይታ እንዳስታወቁት ከመጋቢት ፲ ቀን ፳፻፲3 ዓ/ም ጀምሮ በሀገረ ስብከታቸው ሥር በሚገኙት ማጀቴ፣ አጣዬ፣ ካራቆሬ፣ ጀውሃና ሸዋ ሮቢት አካባቢዎች ቤተ ክርስቲያንንና ኦርቶዶክሳውያንን ዒላማ ያደረገ ጥቃት በአክራሪ ሃይማኖተኞች መፈጸሙን ተናግረዋል፡፡ በጥቃቱም አብያተ ክርስቲያናት ጉዳት ደርሶባቸዋል፤ በርካታ ምእመናንም ተገድለዋል ብለዋል፡፡

ምእመናን በተፈጸመባቸው ጥቃት ምክንያት ሀብት ንብረታቸው እንደወደመና ከመኖሪያ አካባቢያቸው ተፈናቅለው በጊዜያዊ መጠለያ ውስጥ እንደሚገኙ የተናገሩት ሥራ አስኪያጁ ችግሩ አሁን ብቻ የተከሠተ ሳይሆን ከዚህ በፊት መጋቢት ፳፰ ቀን ፳፻፲፩ ዓ/ም ጀምሮ ብዙ ምእመናን፣ ካህናት እንዲሁም አንድ ቤተ መቅደስ የዚህ ችግር ሰለባዎች እንደነበሩ አስታውቀዋል፡፡ በዚያ ወቅት በተከሠተው ችግር ከኀዘን ሳንወጣ በዚህ ወቅት በተመሣሣይ ሁኔታ መጋቢት ወር ፳፻፲3 ዓ.ም በወርሐ

ዐቢይ ጾም አክራሪ ሃይማኖተኞች ከፍተኛ ጥቃትና ወረራ ፈጽመውብናል ሲሉም አክለው ተናግረዋል፡፡

በአሁኑ ሰዓትም በሀገረ ስብከታቸው በሚገኙ አንዳንድ አካባቢዎች የተፈጸመውን ጥቃት ለመቀልበስ ከመንግሥት አካላት ጋር ተቀራርበው በመሥራታቸው በአካባቢው አንፃራዊ ሰላም መኖሩን ያስረዱት ሥራ አስኪያጁ የተፈናቀሉ ምእመናንን ወደ ቀድሞ አካባቢያቸው እንዲመለሱ የማድረግ፣የማጽናናት፣የማረጋጋት፣የማስተማር እንዲሁም አስፈጊውን ዕለታዊ ድጋፍ የማድረግ ሥራ እየተሠራ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

በሸዋ ሮቢት ከተማ ብቻ ከጥቃት የተረፉ ከሁለት ሺህ አንድ መቶ በላይ ተፈናቃዮች ይገኛሉ ያሉት ሥራ አስኪያጁ የአካባቢው አጥቢያዎችም ለእነዚህ ተፈናቃዮች ተመድበው ድጋፍ እያደረጉላቸው መሆኑን ገልጠዋል፡፡ ቤተ ክርስቲያን ያለ ምንም የእምነት ልዩነት ለተፈናቃዮች ድጋፍ እያደረገች እንደምትገኝና ድጋፉም ለስድስት ተከታታይ ቀናት የዘለቀ መሆኑን ያስገነዘቡት ሥራ አስኪያጁ በሞትና በመፈናቀል ከፍተኛውን ቁጥር የያዙት ኦርቶዶክሳውያን ክርስቲኖች ቢሆኑም የእስልምናና የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች ጭምር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተጠልለው እንደሚገኙ አስረድተዋል፡፡ በሀገረ ስብከት ደረጃ ለአጣዬና ለሸዋ ሮቢት ተፈናቃዮች መጠነኛ ድጋፍ መደረጉንም ሥራ አስኪያጁ አክለው ተናግረዋል፡፡

**ይህንን ተግባር ላለፉት አርባና ኀምሳ ዓመታት ይፈጽሙት እንደነበረ ቢታወቅም በተለይ ካለፉት ሦስት ዓመታት ወዲህ መልኩንና ዓይነቱን እየለዋወጡ በቤተ ክርስቲያንና በምእመና ላይ ዘመን የማይሽረው ትውልድ የማይረሳው በደል ሲያደርሱ ቆይተዋል፤ አሁንም እያደረሱ ይገኛሉ፡፡**

እስካሁን ድረስ ከአብያተ ክርስቲያናት የካራ ቆሬ ቅዱስ ጊዮርጊስ ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ ጉዳት የደረሰበት ሲሆን የኩሪ ግሪ ቅዱስ ሚካኤል ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ መጠነኛ ጉዳት እንደደረሰበት ሥራ አስኪያጁ አስረድተው በሌሎች አካባቢዎች ባሉ አብያተ ክርስቲያናት ግን ከሙከራ የዘለለ ጉዳት እንዳልደረሰባቸው አክለዋል፡፡ እስካሁን ድረስ ምን ያህል ምእመናን በአክራሪዎች እንደተገደሉ የተጣራ መረጃ እንደሌለና ጥቃቱን ለመመርመር ሦስት አጣሪ ቡድን ተመድቦ በአጣዬ፣ በማጀቴና በሸዋ ሮቢት የማጣራት ሥራ እየሠሩ መሆኑን ሥራ አስኪያጁ ተናግረዋል፡፡

አያይዘውም "በሀገረ ስብከታችን የፀጥታ ችግር በነበረበት ወቅት አክራሪ ሃይማኖተኞች ዒላማ ያደረጉት ቤተ ክርስቲያንና ምእመናንን ከአካባቢው ለማጥፋት ነበር፤ ነገር ግን ምእመኖቻችን ራሳቸውን መሥዋዕት አድረገው ብዙ አብያተ ክርስቲያናትን ከጥፋት ታድገዋል፤ የደረሱ ጥፋቶችን በአንዝዘ በተደገፈ መረጃ ለመናገር ጥናት የሚያስፈልግ ቢሆንም በጥቃቱ ከፍተኛ የሆነ ጉዳት የደረሰው ግን አጣዬ ላይ ነው፡፡ በአጣዬ ከተማና አካባቢው የከፋ ውድመት ደርሷል፡፡ በማጀቴም እንደዚሁ መለስተኛ ጉዳት ቢደርስም የከፋ ጉዳት እንዳይደርስ ሕዝቡ ተደራጅቶ የመጣውን አክራሪ ኃይል መመከት ችሏል" በማለትም አስረድተዋል፡፡ ሥራ አስኪያጁ አክለውም "ከዚህ ቀደም የችግሩን ስፋትና ጥልቀት የሚያስረዳ ደብዳቤ ለቅዱስ ሲኖዶስ ጽፈናል፡፡ በቀጣይም በጥናት ላይ የተመሠተ የተጣራ መረጃ ለመንግሥት እናቀርባለን" ካሉ በኋላ ለወደፊትም ቢሆን አክራሪዎች በአካባቢው ተመሳሳይ ችግሮችን ሊፈጠሩ እንደሚችሉ በመቆም "ቤተ ክርስቲያንም ሆነች መንግሥት የየድርሻቸውን ሊወጡ ይገባል" ብለዋል፡፡

ቤተ ክርስቲያን አንድነቷን ጠብቃ የመጣባትን ወራሪ ጠላት መመከት ያስፈልጋታል ያሉት ሥራ አስኪያጁ "ባልሆነ ነገር ጊዜያችን በከንቱ የምናሳልፍበት ወቅት ላይ አይደለም፤ በሀገራችን በአራቱም አቅጣጫ ቤተ ክርስቲያንና ምእመናንን ማዕከል ያደረገ አደጋ ከፊታችን መቷል፤ ስለዚህ ከአባቶቻችን ጀምሮ ሁላችንም

በመደራጀትና በመናበብ የመጣብንን አደጋ መቀልበስ ያስፈልጋል" ብለዋል:: መረጃ ከመለዋወጥና ከማደራጀት አንስቶ ቤተ ክርስቲያን የተለየ ሥራ መሥራት እንዳለባት ሥራ አስኪያጁ ጠቁመው በሰሞኑ ጥቃት ምክንያት የተፈናቀሉ ምእመናንን መደገፍ፣ ማፅናናትና ማስተማር እንደሚያስፈልግም ተናግረዋል::

የሰሜን ሸዋ ዞን ዋና አስተዳዳሪ አቶ ታደሰ ገ/ጻድቅ በበኩላቸው "በዞኑ በተለይ በአጣዬ፣ በማጀቴና በሸዋ ሮቢት አካባቢ ከፍተኛ የፀጥታ ችግር በመከሠቱ ምክንያት በርካታ የኅብረተሰብ ክፍሎች ተገድለዋል፤ ቤታቸው ተቃጥሏል፤ ሀብት ንብረታቸው ተዘርፏል፤ እንዲሁም አብያተ ክርስቲያናትም ተቃጥለዋል፤" በማለት ተናግረዋል:: ጥቃት ያደረሰው ይሄው የተደራጀ አክራሪ ቡድን ጥቃቱን የብሔርና የሃይማኖት ለማድረግ እንቅስቄሴ ማድረጉንም አክለው አስረድተዋል::

አክራሪዎች በተለያየ ቦታ በፈጸሙት ጥቃት ሦስት ያህል አብያተ ክርስቲያናት መቃጠላቸውን ያስታወቁት አስተዳደሪው "በአብያተ ክርስቲያናቱ ላይ የተፈጸመው ጥቃት ሆን ተብሎ ሃይማኖትን ከሃይማኖት ጋር ለማጋጨት የተደረገ ሴራ ነው:: በተፈጸመው ጥቃትም የእስልምና እምነት ተከታይ ወገኖች የተገደሉ ቢሆንም ጥቃቱ ይበልጥ የክርስትና እምነት ተከታዮችን ዒላማ ያደረገ መሆኑን የሚያመላክቱ ታላላቅ የኦርቶዶክስ አባቶች በጥይት ተደብድበው መገደላቸው ነው" ሲሉ ተናግረዋል::

ዋና አስተዳዳሪው አያይዘውም "አካባቢው ሁልጊዜም የሥጋት ቀጠና መሆኑ ቢታወቅም ሕዝቡን አደራጅተን ራሱን እንዲከላከል ባለማድረጋችን ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ይህ የታጠቀና የተደራጀ አክራሪ ኃይል ሕዝባችን በመደበኛ እንቅስቃሴ ላይ እያለ ከፍተኛ ጥቃት ፈጽሞበታል" ካሉ በኋላ "የአካባቢው ማኅበረሰብ ሰላምና ደኅንነቱ እንዲጠበቅ ባለፉት ጊዜያት በርካታ ሥራዎችን የሠራን ቢሆንም በአካባቢው የሚንቀሳቀሰው "የኦነግ ሸኔ" ኃይል ባልታሰበ ጊዜ ጥቃት መፈጸሙን አስገንዝበዋል::

ሰላምን አማራጭ አድርጎ በተቀመጠና ምንም ዓይነት ቅድመ ዝግጅት ባላደረገ ማኅበረሰብ ላይ የተፈጸመውን ጥቃት በቀላሉ ለመቀልበስ አስቸጋሪ እንደሆነ አስተዳደሪው ገልጠው "ማኅበረሰቡን በስንቅና ትጥቅ ማደራጀት ብንችል ደግሞ የአካባቢውን ሰላም ከመጠበቅ አልፎ የአጎራባች አካባቢዎችንም ሰላም መጠበቅ የሚችል አቅም አለው" ብለዋል:: በአካባቢው ሕዝቦች መካከል ቁርሾና መጠራጠር እንዳይፈጠርም በጥንቃቄ ሲሠሩ እንደነበር አስተዳደሪው አክለው አስረድተዋል::

ለኦሮሞ ብሔረሰብ ዞንና ለሰሜን ሸዋ ዞን ሲያገለግል የነበረውን የፀጥታ ኃይል ለተልእኮ ወደ ሌላ አካባቢ መዛወሩን እንዳጋጣሚ ተጠቅመው አክራሪ ኃሎች ጥቃቱን እንደፈጸሙ የገለጡት አስተዳደሪው ከዚህ ቀደም በአካባቢው የተፈጸሙ ጥቃቶችን ከግምት ውስጥ ያስገባ ዘላቂ መፍትሔ ለማበጀት ተደጋጋሚ ጥፋቶችንም ለማስቀረት የተቀናጀ ወጥ ሥራ መሥራት እንደሚያስፈልግ በማመን ሥራዎችን እየሠራን ነው ያሉት አስተዳደሪው "በተፈጸመባቸው ጥቃት የተፈናቀሉትና ሀብት ንብረታቸው የወደመባቸውን የኅብረተሰብ ክፍሎች በሥነ ልቦና የማረጋጋትና የመደገፍ ሥራዎችንም በተጓዳኝ እየሠራን እንገኛለን" ብለዋል::

አስተዳዳሪው ከዚሁ ጋር በማያያዝም የዞን አመራሮች በየአካባቢው ተሠማርተው እና መድረኮችን ፈጥረው ከማወያየት ጀምሮ በአካባቢው ተጨባጭ ለውጥ የሚያመጡ ሥራዎች እየተሠሩ እንደሆነ፤ የዓይነትና የጥሬ ገንዘብ ድጋፍ ለማሰባሰብ ኮሚቴ ተቋቁሞ እንቅስቃሴ መጀመሩንም አስታውሰው አስተዳደሪው በአካባቢው የዞን፣ የክልልና የፌዴራል የምርመራ ቡድን ገብቶ ምርመራ መጀመሩንና ከምርመራው በኋላም የችግሩ ምንጪ ምን እንደሆነ በመለየት የተጣራ መርጃ ለሕዝብ ይፋ እንደሚሆን እንዲሁም ለችግሩ የሚመጥን መፍትሔ እንደሚቀመጥለት ተናግረዋል::

ለአማራ ብዙኃን መገናኛ ድርጅት በስልክ አስተያየታቸውን የሰጡ አንድ የአጣዬ ከተማ ኗሪ እንደገለጡት በአካባቢያቸው እጅግ የሠለጠነና ዘመናዊ ትጥቅ ያለው ኃይል ጦርነት ከፍቶ ብዙ ንጹሓንን እንደገደለና ሀብት ንብረት እንዳወደመ ተናግረዋል::

# «ምእመናን በእምነታቸው እንዲጸኑ እኛ ካህናት ትጉህ እረኛ ልንሆን ይገባል»

*- ሊቀ ትጉሃን ደሴ መኮንን*

**በመጽሐፈ ሲራክ**

*የተወደዳችሁ አንባብያን በዛሬው የቤተ አብርሃም ዐምድ ዝግጅታችን ይዘንላችሁ የቀረብነው በጎፋ መካነ ሕያዋን ቅዱስ ገብርኤል ካቴድራል አገልጋይ ካህን የሆኑትን ሊቀ ትጉሃን ደሴ መኮንንን ነው። ሊቀ ትጉሃን ደሴ መኮንን በ ፲፱፻፷፰ ዓ.ም ወደ ካቴድራሉ መጥተው ማገልገል ከጀመሩበት ጊዜ ጀምሮ ዘርፈ ብዙ መንፈሳዊና ሐዋርያዊ አገልግሎትን ሲሰጡ ቆይተዋል አሁንም እየሰጡ ነው። ወንጌል እንዲስፋፋ፣ ምእመናን እንዲበዙ ወደ ተለያየ ቦታ በመዘዋወር ብዙ አብያተ ክርስቲያናትን አሳንጸዋል፤ አሳድሰዋል። በተቀጠሩበት ደብር በቅስና፣ የሰበካ ጉባኤ አባል በመሆን፣ እንዲሁም ለመንፈሳዊ ሥራ በተለያዩ ኮሚቴዎች ውስጥ በመግባት አገልግለዋል።*

*በሁለተኛው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ በብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ ስም ሲሠራ የነበረውን አደባባይ የተለያዩ ምእመናንን በማስተባበር አሠርተዋል። በካቴድራሉ ሰንበት ት/ቤት መንፈሳዊ አገልግሎት ውስጥ ግንባር ቀደም ተሳታፊ ናቸው። ዛሬም ድረስ ቅድስት ቤተ ክርስቲያንንና ምእመናንን የሚጠቅም ዘርፈ ብዙ የልማት ሥራዎችን እየሠሩ ይገኛሉ።*

*አባታችን ከልጅነታቸው ጀምሮ ያላቸውን የአገልግሎትና የሕይወት ተሞክሮ እንዲያካፍሉን እንግዳ አድርገናቸዋል ተከታተሏቸው፦*

*ስምዐ ጽድቅ፦* አባታችን ይህን ቃለ መጠይቅ እንድናደርግ ፈቃደኛ በመሆንዎ በእግዚአብሔር ስም እናመሰግናለን። ስለ ልጅነት ሕይወትዎ ይንገሩን? የት ተወለዱ? የት አደጉ? የእናትና የአባትዎ ስም ማን ይባላል? የቤተሰብዎን ሁኔታ አያይዘው ቢነግሩን።



ሊቀ ትጉሃን ደሴ መኮንን

*ሊቀ ትጉሃን ደሴ መኮንን፦* እኔም ይህን ቃለ መጠይቅ ከእናንተ ጋር እንዳደርግ ስለጋበዛችሁኝ አመሰግናለሁ። የተወለድኩት በአሁኑ ደቡብ ጎንደር ስማዳ ወረዳ ልዩ ቦታው እመሠዋ ደብር በ፲፱፻፴፩ ዓ.ም ነው። አባቴ ካህን ናቸው መምሬ መኮንን ጣሹ ይባላሉ ፤እናቴ እማሆይ አስናቀች በለው ይባላሉ። የልጅነት ሕይወቴን ያሳለፍኩት በዚያው በተወለድኩበት አካባቢ ሲሆን እንደማንኛውም የገጠር ልጅ የቤተሰቦቼን ከብት በእረኝነት በመጠበቅ ነው። በኋላም ወደ አብነት ትምህርት ቤት ገብቼ በዲቁና ማዕረግ ማገልገል እንደጀመርኩ ከአሁኗ የትዳር አጋሬ ወ/ሮ አስጥይው አበጀ ጋር የካቲት ፲፱ ቀን ፲፱፻፶፯ ዓ.ም በሥርዓተ ተክሊል ጋብቻችንን ፈጽመናል። ሰባት ልጆች እና ሰባት የልጅ ልጆች ያደረስኩ ሲሆን ከነዚህ ከሰባቱ ሁለቱ ልጆቼ በሕይወት የሉም።

***ስምዐ ጽድቅ፦*** **ስለ አብነት ትምህርት ቤት ሕይወትዎ ይንገሩን የት የት ተማሩ?**

***ሊቀ ትጉሃን፦*** ትምህርት የጀመርኩት እዚያው የተወለድኩበት እመሠዋ በዓታ ደብር ነው:: በዚያ ከባሕታዊ አባ ገብረ መስቀልና ከአለቃ ወልደ ገብርኤል ከፊደል ጀምሮ ዳዊትን፣ በስማዳ አርባዕቱ እንስሳ ደብር ከመሪጌታ አካል ተፈራ ውዳሴ ማርያም ዜማን ተማርኩ፤ በጋይንት አትከና ጊዮርጊስ ከመሪጌታ ክፍሌ ጾመ ድጓና ምዕራፍ እንዲሁም መዝገበ ቅዳሴን ተምሬ አጠናቀቅሁ:: እነዚህን ትምህርቶች ከተማርኩ በኋላ በ፲፱፻፵፯ ዓ.ም እዚያው ጎንደር ከብፁዕ አቡነ ሚካኤል የዲቁና ማዕረግ ተቀበልኩ::

**በጎ የሕይወት ገጠመኝ ብዬ የምለው እግዚአብሔር አምላክ ፈቅዶልኝ በተለያዩ ቦታዎች ምእመናን የሚሰበሰቡበት፣ ክርስትና የሚነሱበት፣ ንሰሓ የሚገቡበት፣ ሥጋ ወደሙን የሚቀበሉበት እንዲሁም ሲሞቱ በሥጋ የሚያርፉበት አብያተ ክርስቲያናትን ማሳነጽ መቻሌ በሕይወቴ ዘመን ሁሉ እርካታዬና ደስታዬ ነው::**

***ስምዐ ጽድቅ፦*** **ማዕረገ ዲቁናን ከተቀበሉ በኋላ የት የት አገለገሉ? ምን ያህል ጊዜ አገለገሉ**

***ሊቀ ትጉሃን፦*** የዲቁና ማዕረግን ከተቀበልኩ በኋላ አገልግሎት የጀመርኩት በዚያው በተወለድኩበትና ባደኩበት እመሠዋ በዓታ ደብር ነው:: በግንቦት ወር በ፲፱፻፶፯ ዓ.ም እዚያው ጎንደር ከብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ የቅስናን ማዕረግ ተቀበልኩ:: በዚሁ ደብር እና በአካባቢው ባሉ የተለያዩ ደብራት በቅስና መንፈሳዊ አገልግሎትንም ስሰጥ ቆየሁ::

በእመሠዋ በዓታ ደብር በቋሚነት እንዲሁም በአካባቢው ላይ ባሉ ሌሎች ደብራት አልፎ አልፎ በቅስና ማዕረግ ሳገለግል የቆየሁት እስከ ፲፱፻፷፫ ዓ.ም ድረስ ነው:: በዚሁ ዓመት ታኅሣሥ ወር ላይ ከትውልድ ሀገሬ ለቅቄ ወደ ሸዋ ክፍለ ሀገር በመምጣት ዝቋላ አካባቢ እምቦሌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በቅስና ማዕረግ ተቀጥሬ ለአንድ ዓመት ከሦስት ወር አገለገልኩ:: በዚያ ደብር እና አጎራባች በሆኑ ደብራት ላይ በመዘዋወር አስተምር ነበርና ቁጥራቸው ከሦስት መቶ በላይ የሆኑ ኢ-አማንያንን በማስተማር እና በማጥመቅ የሥላሴ ልጅነት እንዲያገኙ አድርጌአለሁ:: እዚያ ግን ብዙ መቆየት አልቻልኩም::

***ስምዐ ጽድቅ፦*** **ለምን? ምንድን ነበረ ምክንያቱ?**

***ሊቀ ትጉሃን፦*** በእምቦሌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን እና በአካባቢው ባሉ አብያተ ክርስቲያናት ላይ የጀመርኩትን ሐዋርያዊ አገልግሎት በስፋት እንዳልሰጥ እንቅፋት ገጠመኝ:: እንደሚታወቀው ወቅቱ ፲፱፻፷፮ ዓ.ም አብዮት የፈነዳበት ፤የአፄ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት የወደቀበት እንዲሁም ሥልጣኑን ከተረከበው የደርግ ወታደራዊ መንግሥት ርዕዮተ ዓለም አንጻር የእኔ አስተምህሮ እንደ ኃጢአት በመቆጠሩ በጊዜው እና ዘመን ባመጣቸው ባለሥልጣናት ወከባው በዛብኝ:: ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ‹‹ከዚያች ከተማ ቢያሳድዱአችሁ ወደ ሌላይቱ ሽሹ›› ማቴ ፲፥፳፫ ባለው አምላካዊ ቃል በዚያ አካባቢ ተዘዋውሬ መንፈሳዊ አገልግሎት መስጠት ባለመቻሌ እና በገጠመኝ ከፍተኛ ተቃውሞ ከሥራዬ በመፈናቀሌ በአቴን ለቅቄ ወደ አዲስ አበባ በመምጣት በጎፋ መካነ ሕያዋን ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ደጅ ጠኝ ሆንኩ:: ከሁለት ዓመት ደጅ ጥናት በኋላም በ፲፱፻፷፰ ዓ.ም በወቅቱ በነበሩት የካቴድራሉ አለቃ መምህር ገብረ

ሚካኤል በኋላ ብፁዕ አቡነ ሣሙኤል መልካም ፈቃድ በቅስና የሥራ መደብ ተቀጥሬ አገልግሎት ጀመርኩ።

***ስምዐ ጽድቅ፦* እስካሁን ድረስ በጎፋ መካነ ሕያዋን ቅዱስ ገብርኤል ካቴድራል እያገለገሉ መሆኑ ይታወቃል ከዚያም በተጨማሪ የተለያዩ ታላላቅ መንፈሳዊ ሥራዎች እንደሠሩ ይነገራልና እስኪ ስለዚያ ይንገሩን?**

*ሊቀ ትጉሃን፦* እውነት ነው እስከ አሁን እዚያ ነው እያገለገልኩ ያለሁት። አገልግሎቴ በቋሚነት እዚያ ይሁን እንጂ ከካቴድራሉ ጀምሮ በተለያዩ ቦታዎች ብዙ የልማት ሥራዎችን ስሠራ ቆይቻለሁ። በካቴድራሉ የሰበካ ጉባኤ አባል ሆኜ ካቴድራሉን ከማሳደስ ጀምሮ በግቢው ውስጥ የተለያዩ ሕንጻዎች ሲሠሩ፣ የግቢው አስፋልት ሲታደስ እንዲሁም በብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ ስም ሊሰየም የነበረው የጎፋ ገብርኤል አደባባይ ሲሠራ ምእመናንን በማስተባበር ገቢ ሳሰባስብ ቆይቻለሁ፤ በካቴድራሉ ውስጥ እጅግ ዘመናዊ መጸዳጃ ቤት አስገንብቻለሁ። ቋሚ የአገልግሎት ቦታዬ ጎፋ ገብርኤል ቢሆንም በተለያዩ ቦታዎች በመዘዋወር ኢ-አማንያንን በማስተማር የሥላሴ ልጅነትን እንዲያገኙ አድርጌአለሁ። አብያተ ክርስቲያናት በሌሉባቸው ቦታዎች በመሄድ ምእመናንን በማስተባበር ብዙ አብያተ ክርስቲያናትን አስተክያለሁ፡ አሁንም አቅሜ በፈቀደ ቤተ ክርስቲያንን እያገለገልኩ እገኛለሁ። ወደፊትም ከዚህ ዓይነቱ መንፈሳዊ አገልግሎት እስከ ሕይወቴ ፍጻሜ አልለይም።

***ስምዐ ጽድቅ፦* ከነዚህ የልማት ሥራዎች ባሻገር ስለ አሳነጹአቸው አብያተ ክርስቲያናት በዝርዝር ይንገሩን**

*ሊቀ ትጉሃን ፦* ከመደበኛ አገልግሎቴ ውጪ ምእመናንን በማስተባበር በተለያዩ ቦታዎች ብዙ አብያተ ክርስቲያናትን አስተክዬ ለምእመኑ አገልግሎት እንዲሰጡ አስደርጌአለሁ። ለምሳሌ፦

- ሐምሌ ፳፫ ቀን ፲፱፻፹፫ ዓ.ም ቅዳሴ ቤቱ የተከበረው የላፍቶ ደብረ ትጉሃን ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን፤ በ፲፱፻፺፩ ዓ.ም ቅዳሴ ቤቱ የተከበረው የኤረር ጎሮ ደብረ ምሕረት ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን፤ ሰኔ ፳፬ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ.ም ቅዳሴ ቤቱ የተከበረው የፉሪ ምስካበ ቅዱሳን ተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን፤ጥር ፳፯ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ.ም ቅዳሴ ቤቱ የተከበረው የመቱ አልዩ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን፤ መጋቢት ፳፰ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ.ም ቅዳሴ ቤቱ የተከበረው የደብረ በረከት ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን፤ጥር ፰ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም ቅዳሴ ቤቱ የተከበረው የፈለገ ዮርዳኖስ መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ ቤተ ክርስቲያን፤ ሰኔ ፳፮ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም ቅዳሴ ቤቱ የተከበረው የዓለም ባንክ አካባቢ የደብረ ራማ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ከአሠራሁአቸው አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ጥቂቶቹ ናቸው።

ከዚህም በተጨማሪ ጎንደር በተወለድኩበት አካባቢ ስማዳ ወረዳ የምትገኘው ታላቋ የበዓታ ደብር ከፍተኛ እድሳት ሲደረግላት በአዲስ አበባ እና በውጭ ሀገር የሚኖሩ የአካባቢውን ተወላጆችና በጎ አድራጊዎችን በማስተባበር ለእድሳቱ ከሚፈለገው ሦስት እጅ የሚሆነውን በደረሰኝ በመሰብሰብ እና በማስረከብ ደብሩ ቀድሞ ከነበረው በተሻለ ሁኔታ እንዲታደስ የበኩሌን አስተዋጽኦ አድርጌአለሁ።

***ስምዐ ጽድቅ፦* በዚህ ሁሉ የአገልግሎት ዘመን ውስጥ የገጠመዎት ጥሩም ሆነ መጥፎ ገጠመኝ ካለዎት ይንገሩን**

*ሊቀ ትጉሃን፦* በሰው ሕይወት ውስጥ ብዙ ገጠመኞች ይኖራሉ። በዚያው ልክ ጥሩ እና መጥፎ ገጠመኞች ይፈራረቃሉ፤ እኔም በነዚህ ሁለት ተቃራኒ ሕይወቶች ውስጥ አልፌአለሁ ስለሁሉም ነገር ግን እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ። በሕይወቴ ውስጥ እጅግ የምደሰትበት እና በጎ የሕይወት ገጠመኝ ብዬ የምለው እግዚአብሔር አምላክ ፈቅዶልኝ በተለያዩ ቦታዎች ምእመናን የሚሰበሰቡበት፣ ክርስትና የሚነሱበት፣ ንስሓ የሚገቡበት፣ ሥጋ ወደሙን የሚቀበሉበት እንዲሁም ሲሞቱ በሥጋ የሚያርፉበት አብያተ ክርስቲያናትን ማሳነጽ መቻሌ በሕይወቴ ዘመን ሁሉ እርካታዬና ደስታዬ ነው።

ሌላው እነዚህን አብያተ ክርስቲያናት እና ሌሎች መንፈሳዊ ሥራዎችን ስሠራ የገጠሙኝ መጥፎ ገጠመኞች መቼም

የምረሳቸው አይደሉም። ጊዜም እንዳልወስድ ከነዚያ ውስጥ ጥቂቱን እናገራለሁ። ቅድም ለመግለጽ እንደሞከርኩት በዝቋላ አካባቢ እምቦሌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን እያገለገልኩ በተጓዳኝ ያላመኑ ምእመናን እንዲያምኑ፣ ያመኑ ክርስቲያኖች እንዲጸኑ ወንጌልን በምሰብክበት ጊዜ በደርግ ወታደሮች ‹‹ዐቢዮቱን የሚቃወም እና ደርግን የሚፃረር›› በሚል ብዙ እንግልት ደርሶብኝ ከሥራ እስከመፈናቀል ደርሻለሁ። በዚያ በደረሰብኝ እንግልትም አካባቢውን ለቅቄ ወደ አዲስ አበባ መጣሁ። አዲስ አበባ መካነ ሕያዋን ጎፋ ገብርኤል ካቴድራል ያለሥራ ለሁለት ዓመት በደጅ ጠኚነት ከተቀመጥሁ በኋላ በቅስና ማዕረግ ተቀጥሬ አገልግሎት ጀመርኩ።

አዲስ አበባ ጎፋ ገብርኤል ካቴድራል በቅስና ባገለግልም ክርስትናን የማስፋፋት፣ ምእመናንን የማብዛት እንዲሁም አብያተ ክርስቲያናትን የማስተከል ሐሳብ ከመጀመሪያው ውስጤ ስለነበረ ወደተለያዩ ቦታዎች በመንቀሳቀስ አብያተ ክርስቲያናትን ለማስተከል እንቅስቃሴ ጀመርኩ። በመጀመሪያም የላፍቶ ደብረ ትጉሃን ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያንን ለማሠራት የተወሰኑ ኮሚቴዎችን ይዤ በየእድሩ እየሄድን ቤተ ክርስቲያኑ ይሰራ ዘንድ ፊርማ እናሰባስብ ነበር። ይህን ያዩት ፀረ ሃይማኖት የደርግ ባለ ሥልጣናት ‹‹ዐብዮቱን ለመቀልበስ የሚንቀሳቀሱ የኢዲዩ ቅጥረኞች በተለይም የጄኔራል ነጋ ተገኝ ዘርና ተልእኮ ፈጻሚዎች ናቸው›› በሚል ሽፋን ተይዘን ወደ እስር ቤት ተወረወርን።

እኔ በታሰርኩበት በዚያ የችግር ወቅት ሥራዬ በመታጎሉና የሚሸፍንልኝም ሰው ባለማግኘቴ ከጎፋ ገብርኤል ካቴድራል ይከፈለኝ የነበረው ደሞዜ ተቋረጠ። በዚህ መሀል ለምግብ የደረሱ ለሥራ ግን ያልደረሱ ልጆቼ እና የቤት እመቤት የሆነችው ባለቤቴ ለችግር ተጋለጡ፤ የሚለብሱት እና የሚበሉት እስኪያጡ የችግር ዶፍ ወረደባቸው። ባለቤቴ ደብዳቤ በመጻፍ ከደብሩ ጀምሮ እስከ መንበረ ፓትርያርክ ድረስ ተንከራተተች፤ እርስዋን ከሕፃናት ልጆቼ ጋር የሚታደግ ግን አልተገኘም። ወደ ቤተ ክርስቲያን በመሄድም ደሞዜን እንዲሰጧት እና ሕፃናቱን ከረኃብ እንድትታደግ ብትለምንም ‹‹የሚሠራው እዚህ ደብር ሲሆን ወደ ሌላ ቦታ የሄደው በጥጋብ ነውና ላልሠራበት አንከፍልሽም›› በማለት ሲመልሱአት አይዞሽ የሚል ረዳት አልነበራትም። ነገር ግን በእግዚአብሔር ቸርነት በጽናት ያንን የመከራ ዘመን አልፈነዋልና እግዚአብሔርን አመሰግነዋለሁ። ምክንያቱም ከዚያ እስር ቤት ስወጣ ተመልሼ አብያተ ክርስቲያናትን ወደ ማሳነጽ ነው የሄድኩት። ሐዋርያው ‹‹ከክርስቶስ ፍቅር ማን ይለየናል? መከራ ነውን? ኀዘን ነውን? ስደት ነውን? ረኀብ ነውን? መራቆት ነውን? ጭንቀት ነውን? መራቆት ነውን ?ሾተል ነውን? ሮሜ ፰፥፴፭ እንዳለው የሚደርስብኝን መከራና ችግር ሳልሰቀቅ ዛሬም ድረስ እግዚአብሔርን እያገለገልኩት እገኛለሁ።

***ስምዐ ጽድቅ፦* አባታችን በመጨረሻ የሚያስተላልፉት ወይም ቀረ የሚሉት ነገር ካለ**

***ሊቀ ትጉሃን፦*** የሰው ልጅ ወደዚህ ምድር የመጣው እግዚአብሔርን ሊያመሰግን፣ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ሊኖር፣ እርሱን ደስ የሚያሰኘውን ሥራ ሊሠራ ነው። እግዚአብሔር አምላክ ለእኛ ካደረገልን አንጻር እኛ ለእርሱ ምንም አላደረግንለትም። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ምድር የመጣው ፣በዚህ ምድር ተመላልሶ ያስተማረው መጨረሻም ሊያድናቸው፣ ሊታደጋቸው መከራ ሞት መቀበሉ ለሰው ልጆች ድኅነት ሲል ነው፤ እኛ ግን እንደ ሐሳቡ አልተመላለስንም ፡ ባስቀመጠን ቦታ አልተገኘንም፣ጊዜ ሞታችንን እያሰብን እንኳ ተዘጋጅተን እየጠበቅነው አይደለም። የክርስቲያን ሥራው ግን ከዚህ ሊያልፍ ይገባዋል እላለሁ። ይልቁንም እኛ ካህናት ድርብ አገልግሎት አለብን ብዙዎቻችን ዛሬ በዐሥራ አምስት ቀን አንዴ የሚሰጠንን የቤተ መቅደስ አገልግሎት ብቻ ይዘን ነው ቁጭ ያልነው። ነገር ግን ወጥተን የእግዚአብሔርን መንግሥት ልንሰብክ፣ ያዘኑትን ልናረጋጋ፣ የታሰሩትን፣ የታመሙትን ልንጠይቅ፣ ልንደግፍ ይገባል። በአጠቃላይ ምእመናን በእምነታቸው እንዲጸኑ እኛ ካህናት ትጉህ እረኛ ልንሆን ይገባል።

***ስምዐ ጽድቅ፦* አባታችን ስለሰጡን ቃለ መጠይቅ በእግዚአብሔር ስም እናመሰግናለን።**

***ሊቀ ትጉሃን፦***እግዚአብሔር ይስጥልኝ እኔም አመሰግናለሁ።

# “የቤተ ክርስቲያንን አስተምህሮ ለመበረዝ በተነሡ ቡድኖች ላይ እስካሁን የተወሰደ ተጨባጭ ርምጃ የለም”

*- ብፁዕ አቡነ ዘካርያስ (የምዕራብ ጎጃም ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ)*

*በካሣሁን ለምለሙ*

*የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን አስተምህሮ ለመበረዝ ከካቶሊክ እስከ ፕሮቴስታንት ከተሐድሶ እስከ ቅባትና ጸጋ እንዲሁም ሌሎች ለዘመናት ጥረት ሲደርጉ ቆይተዋል፡፡ እነዚህ አፅራረ ቤተ ክርስቲያን በውጭ ካሉ ሀገራት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በሚደረግላቸው ድጋፍ በከፍተኛ የሰው ኃይልና ገንዘብ ታግዘው ለዘመናት የቤተ ክርስቲያንን አስተምህሮ ሲሸረሽሩ ምእመናንን ሲያወዛግቡና ሲከፋፍሉ ቆይተዋል፡፡ ቤተ ክርስቲያንም ኃይለ እግዚአብሔርን አጋዥ አድርጋ ከቅጥሯ ውጭ ያሉትን ቀሳጥያን ከቅጥሯ ስታርቃቸው በውስጧ የነበሩ የእናት ጡት ነካሾችን ደግሞ በመምከር፣በማስተማር፣ንስሐ በመስጠት በዚህ ሁሉ አልፈው የማይመለሱትን ደግሞ በማውገዝ ከዐውደ ምሕረቷ እንዳይቆሙ ከቅጥሯ እንዳይደርሱ በማድረግ አስተምህሮዋን ከብረዛ ምእመኖቿን ደግሞ ከነጠቃ ስትታደግ ቆይታለች፡፡ እነዚህ የበግ ለምድ የለበሱ ነጣቂ ተኩላዎች ለጊዜው የተሳካላቸው ቢመስላቸውም የቤተ ክርስቲያንን አሸናፊነትና መለኮታዊ ኃይል መቋቋም ሳይችሉ ቆይተዋል፡፡ የነጣቂ ተኵላዎች ጥረትም ከንቱ ሆኖ ቤተ ክርስቲያን በቻለችው መጠን ከሐዋርያዊ ጉዞዋ ሳትገታ ለዓለም ብርሃን መሆኗን ቀጥላለች፡፡*

*ይሁን እንጂ ዛሬም ድረስ ቦግ እልም የሚሉ ቀሳጥያን ጥንታዊውን የቤተ ክርስቲያናችንን አስተምህሮ ለመበረዝ በአንዳንድ የሀገራችን ክፍሎች የሞት ሽረት ትግል እያደረጉ እንደሆነ እንገነዘባለን፡፡ ቀሳጥያኑ የቤተ ክርስቲያናችንን አስተምህሮ በመጤ አስተምህሮ ለመተካት ደፋ ቀና ከሚሉባቸው አካባቢዎች መካከል የምሥራቅ ጎጃም ሀገረ ስብከት አንዱ ነው፡፡ “የቅባትና ጸጋ እምነት አራማጆች ነን” በማለት በሀገረ ስብከቱ የሚገኙ ምእመናንን ሲከፋፍሉ፣*



ብፁዕ አቡነ ዘካርያስ የምዕራብ ጎጃም ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ

*የቤተ ክርስቲያንን አስተምህሮ ሲሸረሽሩ፣ እውነተኛ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ አባቶችን ሲያዋክቡ፣ ከሥራ ገበታቸው ሲያባርሩ፣ ሲያስገድሉ፣ ዶግማዊ የቤተ ክርስቲያን መጠሪያ የሆነውን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርቲያንን “ተዋሕዶ” የሚለውን በማውጣት ወደ “ጥንታዊቷ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን” ኑ እያሉ ሲያታልሉ እንዲሁም ተዘርዝሮ የማያልቅ ግፍ ሲፈጽሙ ቆይተዋል፡፡ በአሁኑ ሰዓትም የምሥራቅ ጎጃም ሀገረ ስብከትን የብጥብትና የሁከት ቀጠና ለማድረግ በትኩረት እየሠሩ ይገኛሉ፡፡ ጉዳዩ ያሳሰባቸው የሀገረ ስብከቱ ማኅበረ ምእመናን፣ አገልጋይ አባቶች፣ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ርእሰ መስተዳድር ክቡር አቶ አገኘው ተሻገር እንዲሁም የአጎራባች ሀገረ ስብከት ሊቃነ ጳጳሳት ጉዳዩን*

***ለቅዱስ ሲኖዶስ አቅርበው ምላሽ እየተጠባበቁ ይገኛሉ። ቅዱስ ሲኖዶስም የሃይማኖት ጉዳይ ነውና ለችግሩ አፋጣኝ መፍትሔ ይሰጣል ተብሎ ይጠበቃል። ለምሥራቅ ጎጃም ሀገረ ስብከት አጎራባች ከሆኑ አህጉረ ስብከት መካከል የምዕራብ ጎጃም ሀገረ ስብከት አንዱ ሲሆን የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ዘካርያስ ጉዳዩን አስመልክቶ ከማኅበረ ቅዱሳን ቴሌቪዥን ጋር አጭር ቆይታ አድርገዋል። ያደረጉትን ቆይታም ለስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ በሚመች መልኩ ወደ ጹሑፍ ቀይረን እንደሚከተለው አቅርበነዋል። መልካም ንባብ።***

*ስምዐ ጽድቅ፦* **ብፁዕ አባታችን ለቃለ መጠይቁ ፈቃደኛ ስለሆኑ በእግዚአብሔር ስም አመሰግናለሁ።**

*ብፁዕ አቡነ ዘካርያስ፦* ጉዳዩ አሳስቧችሁ አሳቤን እንዳካፍላችሁ ለቃለ መጠይቅ ስለጋበዛችሁኝ አመሰግናለሁ፤ ተባረኩ።

*ስምዐ ጽድቅ፦* **የምዕራብ ጎጃም ሀገረ ስብከት በሀገረ ስብከት ደረጃ የተዋቀረው መቼ ነው? በውስጡስ ምን ያህል አብያተ ክርስቲያናት ይገኛሉ? በአሁኑ ሰዓት የሕዝበ ክርስቲያኑ ሁኔታ ምን ይመስላል? አገልግሎቱስ?**

*ብፁዕ አቡነ ዘካርያስ፦* የምዕራብ ጎጃም ሀገረ ስብከት ራሱን ችሎ በሀገረ ስብከት ደረጃ የተዋቀረው በ፳፻፬ ዓ.ም ነው። ሀገረ ስብከቱ በርካታ ምእመናን፣ ካህናት አገልጋዮች እንዲሁም አጥቢያዎች ያሉበት ነው። በዚህ ሀገረ ስብከት ውስጥ ከ፲፰፻፹፪ (አንድ ሽህ ስምንት መቶ) በላይ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ያሉ ሲሆን በእነዚህ አብያተ ክርስቲያናትም ውስጥ በቤተ ክርስቲያን ትምህርት የበቁና የነቁ ካህናት፣መምህራነ ወንጌልና ሊቃውንት ይገኛሉ። አብዛኛው የአካባቢው ኅብረተሰብ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ በመሆናቸው ከወጣቶች ጀምሮ እስከ አገልጋዮች ድረስ የሚሰጠው አገልግሎት ነፍስን የሚያስደስት የመንፈስ ርካታን የሚጨምር ነው። በሁሉም አጥቢያዎች ወንጌል በበቂ ሁኔታ ይሰበካል፣ ጸሎተ ምህላ ይደረጋል እንዲሁም ሕዝበ ክርስቲያኑን በዕውቀትና በምግባር የሚያንፁ የተለያዩ መርሐ ግብራት ይዘጋጃሉ።

በሀገረ ስብከታችን ይህ ዘመን ያመጣው ጊዜ የወለደው የተሐድሶ እንቅስቃሴ የለም። ዘጠና አምስት በመቶ የሚሆነው የአካባቢው ኅብረተሰብ ኦርቶዶክሳዊ በመሆኑ ከኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ውጭ የሆነ ባዕድ አስተምህሮን አይቀበልም፤ ለዚያም ተገዥ አይሆንም። ምእመኑ ሃይማኖቱን ጠንቅቆ የሚያውቅ በወሬ ሳይሆን የሃይማኖቱን አስተምህሮ በተግባር እየገለጠ የሚኖር በመሆኑ ክፉና በጎውን የሚበጀውንና የማይበጀውን አስተምህሮ ጠንቅቆ ለይቶ የሚያውቅ ነው። ምእመኑ የቀደመችና እውነተኛ የሆነችውን እምነቱን አጥብቆ እንዲይዝ ሌሎች ሊቃውንት ከሚሰጡት ትምህርተ ወንጌል በተጨማሪ እኔም በየወረዳውና በየአጥቢያዎች እየተዘዋወርኩ አስተምራለሁ፤ እመክራለሁ፤ እባርካለሁ። ይህ መሆኑም ሀገረ ስብከቱ በደንብ የተሰናዳ እንዲሆን፣ ብዙ ሊቃውንትንም ማፍራት እንዲቻል ቤተ ክርስቲያንም በልማት እንድታድግ አድርጓል።

ቤተ ክርስቲያን በምታከናውነው የልማት ሥራ ሁሉ ሕዝበ ክርስቲያኑ ከዕለት ወደ ዕለት ክርስቲያናዊ ግዴታውን በበቂ ሁኔታ እየተወጣ ይገኛል። ምእመናን በየጊዜው የሚያደርጉት የገንዘብና የዓይነት ርዳታ ለተቋማት ግንባታ ገቢ ማስገኛ፣ ለጉባኤ ቤቶች ግንባታ፣ ለአዳዲስ አብያተ ክርስቲያናት ግንባታና ለነባር አብያተ ክርስቲያናት ጥገና እየዋለ ይገኛል። ሀገረ ስብከቱ ከተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች በፀጥታ ችግር ምክንያት ተፈናቅለው የመጡ አገልጋዮችን ሳይቀር ተቀብሎ እያስተናገደ ነው። በትምህርት ረገድም ከተለያዩ አካባቢዎች የሚመጡ ተማሪዎችን ተቀብሎ ባሉት ጉባኤ ቤቶች በጥሩ ሁኔታ እያስተማረ ይገኛል። በአጠቃላይ በሀገረ ስብከቱ ሙሉ አገልግሎት አለ፤ በአገልግሎቱም ምእመናንም ሆኑ አገልጋዮች ደስተኞች ነን።

***ስምዐ ጽድቅ፡-* የሀገረ ስብከትዎ አጎራባች በሆነው ምሥራቅ ጎጃም ሀገረ ስብከት ላይ እየተፈጸመ ያለው የዶግማና ቀኖና ጥሰት በተለይ ከቅባት እምነት ጋር ተያይዞ እንዲሁም አስተዳደራዊ በደሎችን በተመለከተ ለቅዱስ ሲኖዶስ ጽ/ቤት ደብዳቤ ጽፈዋል፤ ይህንን ደብዳቤ ለመጻፍ ምን አነሣሣዎት?**

***ብፁዕ አቡነ ዘካርያስ፡-*** የምሥራቅ ጎጃም ሀገረ ስብከት ለእኔ አጎራባች ሀገረ ስብከት ብቻ ሳይሆን ለአሥራ ስድስት ዓመታት ያስተማርኩበት ነው። እዚያ በነበረኝ ቆይታ ብዙ ካህናትን ክህነት ዲያቆናትም ዲቁና የሰጠሁበት ሀገረ ስብከት ነው። በሀገረ ስብከቱ ብዙ ቁም ነገር የሠራሁበት፤ የብርቱ ሊቃውንት መፍለቂያና የጠንካራ ምእመናን መገኛ እንዲሆን ያደረኩት ነው። ነገር ግን ሁኔታውን መለስ ብየ ሳየው እኔ ከዚያ ሀገረ ስብከት ከወጣሁ በኋላ የነበረው እንዳልነበር የተሠራው እንዳልተሠራ ሆኖ መመልከት ጀምሬአለሁ። ነገሮች ሁሉ መሥመራቸውን ስተው የዶግማ፣ የቀኖናና የመልካም አስተዳደር ጉድለቶች የሚስተዋሉበት ሀገረ ስብከት ሆኖ አግኝቸዋለሁ። ይህ የሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ጥሰትና የመልካም አስተዳደር ችግር ለሀገረ ስብከቱ ብቻ ሳይሆን ለአጎራባች አህጉረ ስብከት ጭምር ችግር እየፈጠረ መሆኑን በመረዳቴና ችግሩ ከመባባሱ በፊት መፍትሔ እንዲበጅለት በማሰብ የቤተ ክርስቲያናችን የበላይ አካል ለሆነው ቅዱስ ሲኖዶስ ደብዳቤ ጽፌአለሁ።

ምንም እንኳን አንዱ ሀገረ ስብከት በሌላው ላይ ጣልቃ አይገባም የሚል መመሪያ ቢኖርም አንገብጋቢ የሃይማኖት ጉዳይ በሚኖርበት ወቅት ግን ጣልቃ መግባትን መመሪያው ስለማይከለክል እኔም ጉዳዩ መፍትሔ እንዲያገኝ ለቅዱስ ሲኖዶሱ በጻፍኩት ደበዳቤ ላይ ያለውን ሁኔታ በግልጽ አስረድቻለሁ። ደብዳቤውን ለቅዱስ ሲኖዶስ የጻፍኩት በነበረኝ ሥጋት ብቻ ተነሣሥቼ ሳይሆን ‹‹በቅባት እምነት›› ስም የተደራጁ ኃይሎች የቤተ ክርስቲያንን ሥርዓት ለመሸርሸርና አንድነቷን ለማናጋት ጥረት እያደረጉ ያሉ በመሆናቸውና በሀገረ ስብከታችን ጭምር ገብተው የጥፋት ተልዕኮቸውን ለመፈጸም ሥምሪት ሲያደርጉ በመታዘቤ ነው። ‹‹በቅባት እምነት›› ስም ከተደራጁት ኃይሎች አንደኛው የተሐድሶ ክንፍ ሲሆን ዓላማቸውም የቤተ ክርስቲያንን ሥርዓት መጣስ፣ ልዩነት መፍጠርና እውነተኛውን የቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ በባዕድ አስተምህሮ መበርዝ ነው።

እንደሚታወቀው የምሥራቅ ጎጃም ሀገረ ስብከት ጥንታዊና ታሪካዊ አድባራትና ገዳማት ያሉበት፣ ታልልቅ አባቶችና ሊቃውንት የሚገኙበት፣ በርካታ ምእመናን ያሉበትና ቀደምት የሆነ ሀገረ ስብከት ነው። በዚህ ሀገረ ስብከት እኔ በነበርኩበት ወቅት በጣት የሚቆጠሩ አፈንጋጭ ኃይሎች ከመናራቸው ውጭ ሁሉም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ልጅነት አክብሮ የሚኖርበት ነበር። የነበሩት አፈንጋጮችም ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን እንዳይጥሱና ምእመናንን በባዕድ ትምህርት እንዳይከፋፍሉ በጥንቃቄ ቁጥጥርና ክትትል እየተደረገባቸው በቤተ ክርስቲያን ላይ የከፋ ጉዳት ሳያደርሱ የምእመናን አንድነት ተጠብቆ የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ተከብሮ ነበር የቆየው። በዚህ ወቅት ግን ሀገረ ስብከቱ ድሮ ከነበረው በተቃራኒ በሚያሳዝን ሁኔታ ላይ ይገኛል።

# ዐቢይ ጾም (ጾመ ሁዳዴ)

በእህተ ሚካኤል

*ልጆች! ባለፈው እትማችን በዐቢይ ጾም (በጾመ ሁዳዴ) ውስጥ ከሚገኙ ሳምንታት እና መጠሪያዎቻቸው ውስጥ ‹‹ምኵራብ›› እና ‹‹መጻዕጉ››ን ስያሜያቸውንና ታሪካቸውን ነግረናችሁ ነበር፡፡ መቼም እንዳልረሳችሁት ተስፋ እንዳርጋለን፡፡ እነሆ በዚህ ዝግጅት ደግሞ ስለ ‹‹ደብረ ዘይት›› እና ስለ ‹‹ገብርኄር›› ይዘንላችሁ ቀርበናል ተከታተሉን፡፡*

## 5. ደብረ ዘይት

ልጆች! አምስተኛው የዐቢይ ጾም ሳምንት ‹‹ደብረ ዘይት›› በመባል ይጠራል፡፡ ይህ ቀን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በደብረ ዘይት ተቀምጦ ሳለ ለደቀ መዛሙርቱ ወደዚህች ምድር ዳግመኛ ስለመምጣቱ ፣ስለ ዓለም ፍጻሜ እንዲሁም ስለ ትንሣኤ ሙታን ያስተማረበት ነው፡፡

ልጆች! የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ስለ ደብረ ዘይት ሲናገር፡- ‹‹ደብረ ዘይት የወይራ ዛፍ ያለበት ተራራ ማለት ነው፡፡ ከኢየሩሳሌም በስተ ምሥራቅ ይገኛል፡፡ በደብረ ዘይትና በኢየሩሳሌም መካከል የቄድሮን ሸለቆ ይገኛል፡፡ ከቤተ መቅደስ አደባባይ እስከ ደብረ ዘይት ሰባ አምስት ሜትር ገደማ ነው፡፡ . . . ኢየሱስ በደብረ ዘይት ተቀምጦ ሳለ ስለ ኢሩሳሌም መፍረስና ስለ ዓለም መጨረሻ አስተማረ ማር ፲፫፥፫ ፡፡ . . . እያለ ይዘረዝራል፡፡

ልጆች! ቅድስት ቤተ ክርስቲያንም ይህንን ታሪክ መነሻ በማድረግ የዐቢይ ጾምን አምስተኛ ሳምንት ደብረ ዘይት ብላ በመሰየም ዕለቱን ታከብረዋለች፣ በዕለቱም ስለ ዓለም ፍጻሜ ትምህርት ትሰጥበታለች፡፡ ደብረ ዘይት በዐቢይ ጾም ዕለታት አጋማሽ ላይ የሚገኝ ስለሆነም ‹‹እኩለ ጾም›› በመባል ይጠራል፡፡

ልጆች! ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በደብረ ዘይት ተራራ ተቀምጦ ሳለ ደቀ መዛሙርቱ ወደ እርሱ ቀርበው ‹‹ንገረን ይህ መቼ ይሆናል? የመምጣትህና የዓለሙ ፍጻሜስ ምልክቱ ምንድነው? ማቴ ፳፬፥፫ ብለው ጠየቁት፡፡ ጌታችን ስለ ዓለም ፍጻሜ እና የዓለም ፍጻሜ ከመድረሱ በፊት ስለሚከናወኑ ምልክቶችም አንድ በአንድ ነገራቸው፡፡ ጌታችን ከተናገራቸው (ካስተማራቸው) ምልክቶች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው ፦

1. የሚያስታችሁ እንዳይኖር ተጠንቀቁ፤ ብዙዎች እኔ ክርስቶስ ነኝ እያሉ በስሜ ይመጣሉና ብዙዎችንም ያስታሉ፡፡
2. የጦርነትንም ወሬ ትሰማላችሁ፤ይህ ሊሆን ግድ ነውና ተጠንቀቁ፤ አትደንግጡ፤ ፍጻሜው ገና ነው፡፡
3. ሕዝብ በሕዝብ ላይ መንግሥትም በመንግሥት ላይ ይነሣሉ፡፡
4. በየሀገሩም ረኃብ፣ ቸነፈርም ፥ የምድር መናወጥ ይሆናል፡፡
5. ያን ጊዜም ለመከራ አሳልፈው ይሰጡአችኋል፤ ይገድሉአችኋልም፤ ስለ ስሜም በሰው ሁሉ ዘንድ የተጠላችሁ ትሆናላችሁ፡፡
6. ያን ጊዜም ብዙዎች ሃይማኖታቸውን ይለውጣሉ፤ እርስ በርሳቸውም አሳልፈው ይሰጣጣሉ፤ እርስ በርሳቸውም ይጣላሉ፡፡
7. ብዙዎች ሐሰተኞች ነቢያትም ይመጣሉ፤ ብዙዎቹንም ያስታሉ፡፡
8. ከዐመፅም ብዛት የተነሳ ፍቅር ከብዙዎች ዘንድ

ትጠፋለች፡፡ እስከመጨረሻው የሚታገሥ ግን እርሱ ይድናል፡፡ በአሕዛብ ሁሉ ላይ ምስክር ሊሆን ይህ የመንግሥት ወንጌል በዓለም ሁሉ ይሰበካል፤ ያን ጊዜም ፍፃሜ ይደርሳል፡፡ ማቴ ፳፬፥፬ - ፲፬

ልጆች! በአጠቃላይ አምስተኛው ሳምንት ‹‹ደብረ ዘይት›› ተብሎ የተሰየመበት ምክንያት ጌታችን በተራራው ላይ ተቀምጦ ስለ ዓለም ፍጻሜና ዳግመኛ ስለመምጣቱ ምልክቶች ለሐዋርያት ማስተማሩ እኛም ይህንን በማሰብ ተዘጋጅተን እንድንኖርም ለማሳሰብም ጭምር ነው፡፡

## 6. ገብርኄር

ልጆች! የዐቢይ ጾም ስድስተኛው ሳምንት ‹‹ገብርኄር›› በመባል ይጠራል፡፡ ገብርኄር ማለት ‹‹በጎ፣ታማኝ አገልጋይ›› ማለት ነው፡፡ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የእኛን ሥጋ ተዋሕዶ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ በምሳሌ ካስተማራቸው ትምህርቶች ውስጥ የ‹‹ገብርኄር›› ታሪክ ይገኝበታል፡፡

ልጆች! ወደ ሌላ ሀገር የሚሄድ አንድ ጌታ ባሮቹን ጠርቶ ለእያንዳንዳቸው እንደየ አቅማቸው ገንዘብ ሰጣቸው፡፡ ለአንደኛው አምስት መክሊት ፣ለሁለተኛው ሁለት መክሊት፣ለሦስተኛው ደግሞ አንድ መክሊት ሰጣቸው፡፡ በዚህ በሰጣቸው መክሊት ነግደው፤ አትርፈው እና እጥፍ አድርገው እንዲቆዩት አደራ ሰጥቶአቸው ወደ ሌላ ሀገር ሄደ፡፡

ባሮቹም ጌታቸው እንዳዘዛቸው የተሰጣቸውን መክሊት ነግደው አተረፉበት፡፡ አምስት መክሊት የተሰጠው ነግዶ ሌላ አምስት መክሊት አተረፈ፤ሁለት መልክሊት የተሰጠውም እንዲሁ ነግዶ ሌላ ሁለት መክሊትን አተረፈ፤ሦስተኛው እና አንድ መክሊት የተሰጠው ባርያ ግን የተሰጠውን ገንዘብ ወስዶ በምድር ውስጥ ቀበረው፤ ጌታው ከሄደበት ሀገር እስኪመጣም ምንም ሳያደርግ ቁጭ ብሎ ጠበቀው፡፡

ከብዙ ዘመንም በኋላ ጌታቸው ከሄደበት ሀገር ተመልሶ እነዚያን ባሮች ጠራና ስለሰጣቸው መክሊት ጠየቃቸው፡፡ አምስት መክሊት የተቀበለው ባሪያ ቀረበና ‹‹ጌታ ሆይ አምስት መክሊት ሰጥተኸኝ ነበረ፤ ነግጄበት ሌላ አምስት መክሊት አትርፌያለሁ›› ብሎ ሰጠው፡፡ ጌታውም አንተ በጎ ታማኝ ባርያ በጥቂቱ ታምነሀል በብዙ እሾምሀለሁ ወደ ጌታህ ደስታ ግባ አለው፡፡ ሁለት መክሊት የተቀበለው ባርያም ‹‹ ጌታ ሆይ ሁለት መክሊት ሰጥተኸኝ ነበረ እነሆ ሌላ ሁለት መክሊት አተረፍኩ›› ብሎ ሰጠው፡፡ ጌታውም አንተ በጎ ታማኝ ባርያ በጥቂቱ ታምነሀል በብዙ እሾምሀለሁ ወደ ጌታህ ደስታ ግባ አለው፡፡

አንድ መክሊት የተቀበለው ባርያም መጥቶ ‹‹ጌታ ሆይ ካልዘራህበት የምታጭድ፤ካልበተንክበት የምትሰበስብ፤ ጨካኝ ሰው መሆንህን አውቃለሁ፤ፈራሁም ሄጄም መክሊትህን በምድር ውስጥ ቀበርኩት ይኸው መክሊትህ›› ብሎ የተቀበለውን አንድ መክሊት ለጌታው መለሰለት፡፡ ጌታውም ‹‹አንተ ክፉ ሀኬተኛ ባርያ ካልዘራሁበት እንደማጭድ፤ ካልበተንኩበት እንደምሰበስብ ታውቃለህን? ስለዚህ ገንዘቤን ለለዋጮች አደራ ልትሰጥ ይገባህ ነበረ፡፡ እኔም መጥቼ ገንዘቤን ከነትርፋ እወስደው ነበረ፡፡ አሁንም መክሊቱን ውሰዱበት ዐሥር መክሊትም ላለው ስጡት ላለው ሁሉ ይሰጠዋል ይበዛለትማል ፤ ከሌለው ግን ያው ያለው እንኳ ይወሰድበታል፡፡ የማይጠቅመውን ባርያ በውጭ ወዳለው ጨለማ አውጡት›› አለ ፡፡ ማቴ ፳፭፥፲፬-፴

ልጆች! ባጠቃላይ የዐቢይ ጾም ስድስተኛ ሳምንት ‹‹ገብርኄር›› ተብሎ መሰየሙ ጌታችን ባስተማረው በዚህ ምሳሌያዊ ትምህርት ውስጥ እያንዳንዳችን ከእግዚአብሔር የተሰጠንን ልዩ ልዩ ጸጋ በሚገባ እንድንጠቀምበትና እግዚአብሔርን እንድናገለግልበት እንደሚገባ ለመግለጽ ነው፡፡

ልጆች! በሚቀጥለው ዝግጅታችን ስለቀሩት የዐቢይ ጾም ሳምንታት መጠሪያና ታሪክ ይዘንላችሁ እንቀርባለን እስከዚያው ደህና ሰንብቱ! እናንተም በተሰጣችሁ ጸጋ እግዚአብሔርን ልታገለግሉ ይገባችኋል እሺ ልጆች!

*የእግዚአብሔር ቸርነት፤*
*የእመቤታችን አማላጅነት፤*
*የመላእክት ጥበቃ አይለያችሁ!*

# የሀብታምና እና የድሀ ሥርዓተ ቀብር

**ኪኑኪሩ ከአዲስ አበባ**

ሰው የተፈጠረው ሕያውና መልካም የሆነው የአምላኩ የእግዚአብሔር የክብሩ ወራሽ እና የስሙ ቀዳሽ ሆኖ እንዲኖር ነው። በምድርም ላይ ክቡር፣ ትሁት፣ ባለጸጋ፣ ንጉሥ፣ ጠቢብ ሆኖ እንዲመላለስ ፈቅዶለታል። ሰው ግን ክቡርና ሕያው ሆኖ መኖር የሚችለው ፈጣሪው ያዘዘውን የሚፈጽም ለእርሱም በትሕትና የሚገዛ መሆን ሲችል ነበር። ይህንንም ‹‹መልካምንና ክፉን ከሚያስታውቀው ዛፍ አትብላ፤ ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህ›› ዘፍ ፪፥፲፯ ብሎ አምላኩ ትእዛዝን ሰጠው። ይህን የመገዛቱ ማሳያ የሆነ ትእዛዝ አክብሮ ቢገኝ ሕያው ሆኖ በሥጋውም በነፍሱም መኖር በተቻለው ነበር። ካልታዘዘ ግን የሞት ሞትን እንደሚሞት ታውቋል። ሰው ግን በሰይጣን ምክር ተነሣሥቶ ይሄህን ትእዛዝ ስለጣሰ፤ ‹‹አትብላ›› ከተባለውም ወስዶ ስለበላ በሥጋም በነፍስም ሞት መጣበት። ከሞት ጋርም መራቆት፣ ሐዘን፣ ትካዜ፣ ሰቆቃ፣ መለየት፣ ውርደት፣ ስደት ደረሰበት።

> **ሞትን ማድነቅ በክርስትና አይፈቀድም። ሞት የተሸነፈ፤ ሥልጣኑንም ያጣ ስለሆነ የሞተን ሰው ከልክ በላይ በማዘን አንሸኝም። የእርሱ ክብሩ መቃብሩ እንደሆነ በማሰብ ቀብርን አናደምቅም። ክርስትና ትኩረቱ ለሟች በሚደረግ ጸሎተ ፍትሐት ላይ ነው።**

ቸር የሆነው እግዚአብሔር የሰውን መጸጸት ተመልክቶ ከአምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን በኋላ የድንግል ማርያምን ሥጋ ተዋሕዶ በተገለጸው በአንድ ልጁ ቤዛነት ሰውን ከሞተ ነፍስ አዳነው። ከነፍስ ሞት ታደገን በትንሣኤው በትንሣኤ ዘጉባኤ ለሚሆነው ለሥጋ ትንሣኤያችን ተስፋ ሰጠን።

ሰው የሥጋ ሞት ያለበት ቢሆንም በታላቅ ክብር የተፈጠረ መሆኑን ስለሚያውቅ ሲሞት ሥጋውን በክብር ማሳረፉ ከቀደመ ዘመን ጀምሮ ያለ ነው። የሰው ሥጋ እንደ እንስሳት በከንቱ አይጣልም። አጽመ ቅዱሳን አውሬ እንዲበላው፣ እንዲጣል፣ እንዲረጋገጥ፣ እንዲናቅ፣ እንዲገፋ አይደረግም። እግዚአብሔርን የሚያምኑ ሰዎች የሰውን ክብር ስለሚያውቁ ሰው ሲሞት ለጊዜው ከእነርሱ ስለመለየቱ አዝነው አልቅሰው በክብር ይቀብሩታል። እግዚአብሔርን በማመን ጸንተው የነበሩ እስራኤላውያንና የቀደሙ አባቶቻቸው በዚሁ መንፈስ ወገኖቻቸውን በክብር ይቀብሩ እንደነበር መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል ፩ኛ ነገሥት ፲፫፥፴፩።

አብርሃም ሚስቱ ሣራ በሞተች ጊዜ ሊያዝንላትና ሊያለቅስላት ተነሥቷል። ከዚያም በኋላ ለኬጢ ልጆች ሚስቱን በክብር የሚያሳርፍበት የቀብር ቦታ በጠየቃቸው ጊዜ እንደ ምኞቱ እንዲሆንለት ‹‹ጌታ ሆይ ስማን አንተ በእኛ መካከል ከእግዚአብሔር ንጉሥ ነህና ከመቃብር ሥፍራችን በመልካም ቦታ ሬሳህን ቅበር፤ ›› ዘፍ ፳፫፥፮ ብለውት ነበር። ከዚያም በኬብሮን ድርብ ስፍራ ያላትን የዋሻ ውስጥ መቃብር መርጦ በዋጋም ገዝቶ ሣራን በዚያ ቀበራት። ያም ሥፍራ የቤተሰቡ ሁሉ መቃብር ሆኖ ያገለግል ነበር። ዘፍ ፳፫፥፲፮-፳ ።

ሰዎች የሞተን ሰው ካላቸው ፍቅርና ከሚገባው ክብር የተነሳ በልዩ ልዩ መንገድ ይቀብሩ፣ ሬሳውንም ያከብሩ ነበር። ሰዎች የሰውን ሬሳ ያጥቡ ነበር።(የሐዋ ፱፥

፴፮) ቅባት ይቀቡት ነበር፤ ቅመም ጨምረው በልብስ ይከፍኑታል። በመግነዝ ይገንዙታል፤ ፊቱን በጨርቅ ይሸፍኑታል፤ (ማር ፲፮፥ ፩፤ ዮሐ ፲፱፥ ፵) በየዘመኑ ክብር ነው በሚሉት መንገድ ይቀብሩ ነበር። ሰውን ከዓለት በተወቀረ ድንጋይ ውስጥ ይቀብሩ ነበር። (ማቴ ፳፯፥ ፷) በኖራ በተቀባ ድንጋይም ይቀብሩ ነበር። መቃብሮቻቸውም ያስጌጡ ነበር። (ማቴ ፳፫፥ ፳፮) ሳያውቅ ካልሆነ በስተቀር በሰዎች መቃብር ላይም ሰው አይረማመድም (ሉቃ ፲፩፥ ፵፬)።

በሐዲስ ኪዳን ደግሞ ተስፋ ትንሣኤን ስላገኘን ለክርስቲያኖች ለሚች የሚደረግ ሐዘንና ለቀብር የሚሰጠው አስተያየት ከክርስትና አስተምህሮ የመነጨ ነው። ሞትን ማድነቅ በክርስትና አይፈቀድም። ሞት የተሸነፈ፤ ሥልጣኑንም ያጣ ስለሆነ የሞተን ሰው ከልክ በላይ በማዘን አንሸኝም። የእርሱ ክብሩ መቃብሩ እንደሆነ በማሰብ ቀብርን አናደምቅም። ክርስትና ትኩረቱ ለሚች በሚደረግ ጸሎተ ፍትሐት ላይ ነው። እግዚአብሔር በክብር ነፍሱን እንዲቀበላት የሚደረገው ተማጽኖ ላይ ነው። በየጊዜውም የሙቱን ስመ ክርስትና እየጠራን በመታሰቢያው ቀን ስለምናደርገው ጸሎት ነው። ቀብር ስንፈጽምም ስናዝንም ሐዋርያው ‹‹ወንድሞች ሆይ ተስፋ እንደሌላቸው እንደ ሌሎች ደግሞ እንዳታዝኑ አንቀላፍተውም ስላሉት ታውቁ ዘንድ እንወዳለን፤ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሞተና እንደተነሣ ካመንን እንዲሁ በኢየሱስ ያንቀላፉትን እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ያመጣቸዋል።›› ያለውን ቃል አንረሳም። /፩ኛ ተሰ ፬፥፲፫/።

አሁን አሁን ግን በቀብር ሥነ ሥርዐት ላይ የሚታዩ አንዳንድ ሁኔታዎች አማንያን በሞት ላይ ያላቸው አመለካከት እየተደበላለቀ መምጣቱን ይጠቁማል። በአንድ በኩል የተጋነነ ሥርዓተ ቀብር ይታያል፤ በሌላ በኩል ደግሞ እንደ ነገሩ የሆነ ሥርዓተ ቀብር ይታያል። በክርስቲያን ሚቾች መካከል በሚደረግላቸው የተጋነነ ሥርዓተ ቀብር ወይም የፍትሐት ሥነ ሥርዓት ልዩነት እየታየ መምጣቱ ያልተገራ አስተሳሰብ የመኖሩ ማሳያ ነው።

የሞተው ሰው ከሞተ በኋላ ሌላ የሚከብርበት ትንሣኤ እንደሌለው በሚያስመስል ሁኔታ ባለ በሌለ ኃይል ቀብሩን ማድመቅና ከፍ ከፍ ማድረግ ጎልቶ ይታያል። ለቀብርም ከፍተኛ ወጪዎችን ማውጣት የተለመደ ሆኗል። ሬሳ የሚቀበርበት ሳጥን የሚዘጋጅበት መንገድም ሆነ የሚቀርበት ዋጋ ሚቹን ከሞት ይመልሰው ይመስል በእጅጉ ውድ እየሆነ ነው። ድሆች የሚቀበሩበትን ሳጥን በአቅማቸው ማግኘት የማይችሉበት ደረጃ ላይ ተደርሷል። ለቀብር አስፈጻሚዎች፣ ለቀብር ማድመቂያና ማክበሪያ ለሚዘጋጁ አበባ ጉንጉኖች፣ የቀብር ሥነ ሥርዓትን እንደ ሠርግ ቀርጸው ቪዲዮ የሚያዘጋጁበት ወዘተ ነገሮች ሲታዩ ቀብርን ማድመቅና ለሐዘን መደገስ ተበራክቷል።

በሌላ በኩል ችግረኞች ቀብር ዕዳ እየሆነባቸው ነው። መቀበሪያ ሳጥን፣ ለሐዘን የሚቀመጡበት የሚጽናኑበት በቂ ስፍራ፣ እንግዶችን የሚያስተናግዱበት እህል ውሃ በማጣት በሰቀቀን ሬሳቸውን የሚቀብሩ እጅግ ብዙ ናቸው። የተቀማጠሉ መቃብሮች ባሉበት እንዲሁ ሬሳቸውን እንኳን ከአፈር ለማገናኘት ጭንቀት ውስጥ የወደቁ ብዙ ናቸው።

የተጋነነ የቀብር ሥነ ሥርዓት ተስፋ ትንሣኤን የረሳን ስለሚያስመስልና ከንቱ ውዳሴን የመናፈቅ ነገር ስለሆነ መታረም ያለበት ነው። በተቻለ መጠን እኩል መጥቶ በሚወስደን ሞት ሳንበላለጥ በሥርዓተ ቀብር ለመበላለጥ መሞከር ትዝብት ላይ የሚጥል ነው። ራስን ማታለል ሆኗል። ስለዚህ ክርስቲያናዊ በሆነ መንገድ ቀብርን የማቀማጠልና ቀብርን የማጎስቆል ሁለት ተቃራኒ ነገሮችን ማጣጣም አለመቻሉም የሚያስተዛዝብ ይሆናል። ይህ ሁኔታ ከፍተኛ ሥነ ልቦናዊ ጫናና የልብ ስብራት የሚፈጠርባቸው ሰዎች ስላሉ መፍትሔ የሚፈልግ ጉዳይ ነው። በተለይ ካህናት ሁሉንም ወገን ስለሚያገለግሉ በተቻለ መጠን ሥርዓት የያዘ፣ ከልኩ ያላለፈ ከልኩም ያልወረደ የቀብር ክዋኔ እንዲኖር ከየቤተሰቡ ጋር መምከር ይጠበቅባቸዋል። ይህ ነገር በካህናት አገልጋዮችና በምእመናንም ላይ በሚሰጡት ግምትና አንዱን ከአንዱ የሚያበላልጡበት ሁኔታ ሲፈጠር መተዛዘቦችና ትችቶች ስለሚያስከትል ‹‹ሳይቃጠል በቅጠል›› በመቃብር ስፍራዎች፣ለሞተ ሰው በሚደረገው የፍትሐት ሥነ ሥርዓት በመሳሰሉት የሚታዩት ልዩነቶች እና የተጋነኑ ነገሮች ያስወግዱ ዘንድ ቤተ ክርስቲያን ልጆቿን ልታስተምር ይገባል።

# ስለ ድንግልናዬ እፍራለሁ

*ውድ የስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ አዘጋጆች እንደምን ከረማችሁ? ስሜ ወለተ ሥላሴ ይባላል የምኖረው አዲስ አበባ ሲሆን የምተዳደረው በንግድ ሥራ ነው። በሥራዬ ጸባይ ምክንያት ከብዙ ሰዎች ጋር እገናኛለሁ። በዚህ ግንኙነት ውስጥም በንግዱ ሥራ ከተዋወቅሁት ሰው ጋር የፍቅር ግኑኝነት ጀምሬ ነበር። ይህ ግንኙነት እድጎ ብዙ ጊዜያችንን የምናሳልፈው አንድ ላይ ሆነ፤ በዚህ ብቻም ሳንወሰን ወደ ግበረ ሥጋ ግንኙነት ገብተን በዚያ አጋጣሚ ድንግልናዬን ለማጣት በቃሁ።*

*ውድ የስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ አዘጋጆች! ከዚያ የፍቅር ጓደኛዬ ጋር ብዙ መዝለቅ ባለመቻላችን ግማሽ መንገድ እንደተጓዝን ተለያየን። በዚህም ምክንያት እጅግ ተጎድቼ ስለነበር ለብዙ ጊዜ የወንድ ጓደኛ ሳልይዝ ቆይቻለሁ። ከጊዜ በኋላ ከሌላ የወንድ ጓደኛ ተዋወቄ ትዳር ለመመሥረት ተስማማን። ካለፈው ጊዜ ትምህርት ስለወሰድኩ ከአሁኑ ጓደኛዬ ጋር ያለኝ ግንኙነት የተቆጠበና ጥንቃቄ የተሞላበት ነው። በዚህም በወንድ ጓደኛዬ ዘንድ ድንግል እንደሆንኩ ተቆጥሬያለሁ። ስለጋብቻችን ስናወራም በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ነው የምንጋባው ይለኛል። ውድ የስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ አዘጋጆች! ለወንድ ጓደኛዬ የቀደመ ሕይወቴን፣ ድንግል አለመሆኔን መናገር አልቻልኩም፤ ከዚህም በተጨማሪ በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ነው የምንጋባው ስላለኝ ኃጢአተኛ ሆኜ እንዴት በእግዚአብሔር ፊት እቆማለሁ የሚለው ያሰጋኛል። ድንግል ያለመሆኔን ሳስብ በሁለት መንገድ ፍርሃቴ ይጨምራል። እጅግ ተቸግሬአለሁና ምን ትመክሩኛላችሁ።*

ውድ እኅታችን ወለተ ሥላሴ ለጥያቄሽ መልስ አገኛለሁ ብለሽ ወደእኛ ጥያቄሽን ይዘሽ በመምጣትሽ እንዲሁም ጥያቄሽን ሳትሸሽጊ በግልጽ በመጠየቅሽ እናመሰግንሻለን። ‹‹በሽታውን የደበቀ መድኃኒት አይገኝለትም›› እንዲሉ አባቶቻችን። እኛም ከጥያቄሽ ተነስተን መልስ ለመስጠት እንሞክራለን። ወለተ ሥላሴ በጥያቄዎችሽ ውስጥ መንፈሳዊ ሕይወት ላይ ያለሽን ዕውቀት አብረሽ ብትገልጪልን ጥሩ ይሆን ነበረ። ሆኖም ጥያቄሽ ላይ ተመሥርተን የሚከተለውን መልስ እንሰጥሻለን።

ወለተ ሥላሴ አንቺው እንደነገርሽን ትዳር ለመያዝ ስትፈልጊ ያስጨነቁሽ ሁለት ነገሮች እንዳሉ ከጥያቄሽ ለመረዳት ችለናል። ድንግል አለመሆንሽን ለወደፊት የትዳር አጋርሽ አለመንገርሽ እና የኃጢአተኛነት ስሜት ስለሚሰማሽ በእግዚአብሔር ፊት ለመቆም መፍራትሽ ነው።

ውድ እኅታችን ሰዎች በተለያየ ምክንያት ድንግልናቸውን ሊያጡ ይችላሉ። አንደኛው እና በብዛት የሚታወቀው ከተቃራኒ ጾታዎች ጋር በሚኖራቸው ከልክ ያለፈ ግኙኝነት ለእንደዚህ ዓይነት ስሕተት መጋለጣቸው ነው። ሁለተኛው ሰዎች በተፈጥሮ ድንግልናቸውን ሊያጡ ይችላሉ። በእርግጥ አንቺ እንደነገርሽን ድንግልናሽን ያጣሽው ከወንድ ጓደኛሽ ጋር በነበረሽ ተራክቦ ነው። በሰዎች ላይ እንዲህ ዓይነት ስሕተቶች ይከሰታሉና አንቺም ይህን አንድ ጊዜ የተፈጸመ ስሕተት በመጀመሪያ እንደስሕተት ተቀብለሽ እና በደል መሆኑን አውቀሽ ንስሓ ልትገቢ ይገባል። እግዚአብሔር አምላክ እጅግ ርህሩህ አምላክ፣ ሁሉንም በቸርነቱ የሚያኖር መሆኑን አውቀሽ ወደ እርሱ መጠጋት ይገባሻል። በውስጥሽ ይዘሽ የኖርሽውን እና ዘወትር የሚያስጨንቅሽን ነገር አውጥተሽ ለካህን በመንገርሽ ሰላማዊ ኑሮን እንድትመሪ ከማድረጉም በላይ ለቀጣይ ሕይወትሽ መስተካከልም ዋስትና ነው።

እንዲሁም በወደፊት የትዳር አጋርሽ እና በአንቺ መካከል ምንም ዓይነት ድብብቆሽ ሊኖር አይገባም። ብዙ ጊዜ በጥንዶች

መካከል የሚኖረው ትዳር የሚፈርሰው፤ ባይፈርስም እንኳ በቤታቸው ውስጥ ሰላም የሚታጣው ሁለቱ ተቃራኒ ጾታዎች በእጮኝነት ዘመናቸው አንዱ ለሌላው መንገር የሚገባውን ነገር ሳይነግረው ሲቀር (በመካላቸው የተሸሸገ ነገር ሲኖር) ከትዳር በኋላ የተደበቀው ነገር ሲታወቅ የሚፈጠረው አለመተማመን ነው፡፡ በመሆኑም አንቺም የነገው ትዳርሽ እንዲቃናና ሰላማዊ ኑሮን ለመምራት እንዲያስችላችሁ የወደፊት የትዳር አጋርሽ ስለአንቺ ማወቅ የሚገባውን ነገር ሁሉ ልትነግሪው ይገባል፡፡ ያለፈ ሕይወትሽን በደሎች በንስሓ መታጠብሽን፣ ዛሬ ላይ አዲስ ሰው መሆንሽን እና ከእርሱ ጋር ባላችሁ ግንኙነት ሰላማዊ ኑሮን ለመመሥረት እንደምትፈልጊ ጭምር ልትነግሪው ይገባል፡፡ እርሱም ቢሆን አንቺ ልታውቂው የሚገባው ነገር ሁሉ ላንቺ መንገር ይጠበቅበታል፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ግልጽ ውይይት ወደፊት በሚኖራችሁ የትዳር ሕይወት ውስጥ መሠረት የሚሆንና መተማመንን የሚፈጥር ነው፡፡

ሁለተኛው በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ለምትፈጽሚው ጋብቻ በእግዚአብሔር ፊት እንዴት እቆማለሁ የሚለው ፍርሃትሽ ነው፡፡ በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሁሉን በንስሓ የሚቀበል ቸር አምላክ አባታችን ነውና በዚህ መንገድ ልትረጂ ይገባል፡፡ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ጋብቻን በተመለከተ የራስዋ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ አላት፡፡ ስለዚህም የወደፊት የትዳር አጋርሽ የጋብቻ ሥርዓቱ በቤተ ክርስቲያን እንዲፈጸም መፈለጉ የተቀደሰ ሐሳብ ነውና ልትደግፊው ይገባል፡፡

በዚህ የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ውስጥ በሥርዓተ ተክሊል የሚጋቡ ጥንዶች በመጀመሪያ ንጽሕናቸውን ጠብቀው በድንግልና ሊኖሩ ይገባል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የንስሓ አባት ሊኖራቸው እና ስለ ጋብቻቸው እንዲሁም ስለሌላው ሕወታቸው ንስሓ ሊገቡ እርስ በርሳቸውም ሆነ ከንስሓ አባታቸው ጋር መመካከርም ይጠበቅባቸዋል፡፡

በቤተ ክርስቲያን ‹‹ተክሊል›› ማለት ክብር ማለት ሲሆን ከለለ፣ አከበረ፣ ጋረደ ከሚለው ግስ የወጣ ሲሆን በተክሊል ሁለቱ ጥንዶች ጽኑ ኪዳን (የማይፈርስ ውል) የሚቀበሉበት ስለሆነ በሥርዓተ ተክሊል የሚደረግ ጋብቻ የከበረ ነው፡፡ ‹‹መጋባት በሁሉ ዘንድ ክቡር ነው፥መኝታውም ርኵሰት የለውም፤›› እንዳለ ቅዱስ ጳውሎስ በዕብራውያን መልእክቱ ምዕራፍ ፲፫ ፥፬፡፡ ተክሊል በቤተ ክርስቲያን የከበረ፣ የተቀደሰ ሁለቱን ጥንዶች እስከ ሞት ድረስ ሳይለያዩ እንዲኖሩ የሚያደርግ ውል ነው፡፡

**ብዙ ጊዜ በጥንዶች መካከል የሚኖረው ትዳር የሚፈርሰው፤ ባይፈርስም እንኳ በቤታቸው ውስጥ ሰላም የሚታጣው ሁለቱ ተቃራኒ ጾታዎች በእጮኝነት ዘመናቸው አንዱ ለሌላው መንገር የሚገባውን ነገር ሳይነግረው ሲቀር (በመከላቸው የተሸሸገ ነገር ሲኖር) ከትዳር በኋላ የተደበቀው ነገር ሲታወቅ የሚፈጠረው አለመተማመን ነው፡፡**

ሌላው ‹‹ተክሊል›› ማለት ‹‹መቀዳጀት›› ማለት ሲሆን ሁለቱ ጥንዶች በጋብቻ ሥርዓታቸው ቀን በራሳቸው ላይ የሚደፉት አክሊል ነው፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ በዕለቱም ለሙሽሮቹ ጸሎትና ሥርዓት ቁርባን የሚፈጸም ሲሆን ሥርዓቱ ‹‹ሥርዓተ ተክሊል›› ይባላል፡፡ ይህ ሥርዓት በሚፈጸምበት ጊዜም ጸሎቱ በጆሮ የሚሰማ፣ አክሊሉ፣ ልብሱ በዓይን የሚታይ ቢሆንም በሙሽሮቹ ላይ የሚያድረው በረከት እና ጸጋ ግን በዓይን የማይታይ፣ በእጅም የማይዳሰስ ረቂቅ ነውና ሥርዓቱ ‹‹ምሥጢረ ተክሊል›› ይባላል፡፡

በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ተክሊል የሚፈጸመው ንጽሕናቸውን ጠብቀው፣ በድንግልና ጸንተው ለኖሩ ጥንዶች ብቻ መሆኑን በፍትሐ ነገሥት ሲገልጽ፤ ከሚጋቡት አንዱ ድንግል ቢሆን ሥርዓተ ተክሊል ይፈጸምለታል የሚል አንቀጽ ፳፬ ቁጥር ፱፻፮ ላይ ተደንግጎ እናገኛለን። በሥርዓተ ተክሊል ለሚጋቡ ሰዎች ሥርዓተ ተክሊል ይፈጸማል፣ ወንጌል ይነበባል፣ ቅብዐ ሜሮን ይደረግላቸዋል። በቃል ኪዳን ቀለበታቸውም ላይ ጸሎት ተደርጎ የመጨረሻውን ሥርዓት ቅዱስ ቁርባንን በመቀበል ጋብቻቸውን ያትማሉ። ይህም ሥርዓት ለሁለቱ ጥንዶች በንጽሕና በድንግልና ተወስነው ለመኖራቸው መገለጫ ነው።

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ንጽሕናቸውን ጠብቀው ለኖሩ ሰዎች እንዲህ ዓይነት ሥርዓት ስታደርግ ድንግልናቸውን በልዩ ልዩ ምክንያት ላጡ ሰዎች ደግሞ ‹‹የመዓስባን ጸሎት›› ወይም ‹‹ጸሎተ አስተሥርዮ›› ታደርግላቸዋለች። ጸሎተ አስተሥርዮ ማለት የይቅርታ (የንስሓ) ጸሎት  ማለት ሲሆን  ድንግልናቸውን በተለያየ ምክንያት ያጡ ሰዎች ኃጢአታቸውን እግዚአብሔር  ይቅር እንዲላቸው የሚጸለይ ጸሎት ነው። በቀኖና ቤተ ክርስቲያንም ድንግልናውን ያጣ ሰው ሥርዓተ ተክሊል እንዳይደረግለት፤ ከሌላጋራ የምትሆነው ሁተኛይቱ ግቢ ግን ከፊተኛይቱ ታንሳለች ስለዚህም የማስተሥረያ ጸሎት ያድርጉ እንጂተክሊል እንዳይደርስላት በሕግ ተጻፈ ይላል። ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፳፬ ቁጥር ፳፻፴፬። በጥንዶች መካከል በድንግልና ምክንያት ልዩነት ካለም ሥርዓተ ተክሊሉ የሚደረግለት ድንግል ለሆነው ብቻ እንደሆነ በፍትሐ ነገሥት ፳፬ ቁጥር ፱፻፮ ተጠቅሶ ይገኛል። ከነዚህ ሕጎች ውጪ በሥርዓተ ጋብቻ ጊዜ ሥርዓተ ቁርባንን በመቀበል ድንግል የሆኑትም ሆነ ያልሆኑት እኩል ይቀበላሉ ማለት ነው።

ወድ እኅታችን ወለተ ሥላሴ ከላይ ስለ ሥርዓተ ጋብቻ በጥቂቱ ለመዘርዘር እንደሞከርነው በመጀመሪያ ከወደፊት የትዳር አጋርሽ ጋር ያለውን ነገር በግልጽ ከተወያያችሁ በኋላ ንስሐ አባት በመያዝ ንስሓን መቀበል እና መመካከር ይገባሻል። እንደ የትዳር አጋርሽ ምኞት ሥርዓተ ጋብቻችሁን በቤተ ክርስቲያን ለማድረግ ስምምነት ላይ መድረስ ይጠበቅባችኋል። ምክንያቱም ከዚያ ጋር ተያይዞ ንስሐ መግባት መዘጋጀት፣ በእምነት መቀበል ያስፈልጋልና ነው። ሥርዓተ ጋብቻችሁን በቤተ ክርስቲያን ማድረግ ስምምነት ላይ ከደረሳችሁ በኋላ በቤተ ክርስቲያን በሚኖረው ሥርዓተ ጋብቻችሁ ድንግል ያልሆንሽው አንቺ ብቻ ከሆንሽ ለባለቤትሽ ብቻ ተክሊል እና ከተክሊሉ ጋር የተያያዘው ጸሉት ሲደረግለት ላንቺ ደግሞ ተክሊል ሳይደረግልሽ ‹‹የመዐስባን ጸሎት›› ወይም ‹‹ጸሎተ አስተሥርዮ›› ይደረግልሻል። በመጨረሻም ሁለታችሁም አንድ የምትሆኑበትን ሥርዓተ ቁርባን በአንድነት ትቀበላላችሁ ማለት ነው።

**በጥንዶች መካከል በድንግልና ምክንያት ልዩነት ካለም ሥርዓተ ተክሊሉ የሚደረግለት ድንግል ለሆነው ብቻ እንደሆነ በፍትሐ ነገሥት ፳፬ ቁጥር ፱፻፮ ተጠቅሶ ይገኛል።**

ስለዚህ እኅታችን ከላይ በዝርዝር ለማንሳት እንደሞከርነው ያለፈ ሕይወትሽን በደሎች በንስሓ አስወግደሽ እና ለአዲሱ ትዳር እራስሽን ማዘጋጀት ይጠበቅብሻል። ከወደፊት የትዳር አጋርሽ ጋር ምንም ሳትፈሪና ሳትሳቀቂ በመወያየት እና በመግባባት እንዲሁም ንስሓ በመግባት የወደፊት ሕይወታችሁን የምትመሩበትን መንገድ መወሰን ይጠበቅባችኋል።  የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት በመጠበቅም በእግዚአብሔር ፊት በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ማግባት ትችያለሽ ማለት ነው። ወለተ ሥላሴ! ሕይወትሽ ተስተካክሎ፣ ያሰብሽው ተፈጽሞ ለዚያ ታላቅ ቀንም እንዲያበቃሽ ጸሎታችን ነው።